# ምዕራፍ 8

# መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

## አጀማመሬና ተሳትፎዬ

የእኔ ታሪክ ከመሠረት ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጋር በጣም የተሳሰረ ስለሆነ በዚች ቤተ ክርስቲያን ምስረታና አስተዳደር የነበረኝን ተሳትፎ መግለጽ ጥሩ ይመስለኛል። በሜኖናይት ሚስዮንም ሆነ በመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተቀጥሬ ሠርቼ አላውቅም፡፡ ከሚስዮኑ ጋር ግንኙነቴ የተጀመረው ደደር ትምህርት ቤት ነው፤ ከዚያም በኋላ ለስምንት ሳምንታትም ቢሆንም በናዝሬት ኃ. ማ.ማ.መታሰቢያ ሆስፒታል ይካሄድ በነበረው ድሬሰርና መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የነበረኝ ቆይታ ነው። የድሬሰር ትምህርቴን አቋርጬ ከጸጋ ወ/ማርያም ጋር ተግባረ ዕድ ት/ቤት መግባቴን በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ገልጬአለሁ፡፡ አዲስ አበባ ሆኜ መርሃ ዕዉራን ት/ቤት አየሄድሁ የእሁድ ፕሮግራም በመሳተፌ በዚያ የክርስትና ሕይወቴ እንደተጠናከርልኝ አትቼአለሁ። ከተግባረእድ ት/ቤት ከተመረቅሁ በኋላ ከእነ በየነ ጭምጭአይበሉ ጋር በዚያው ግቢ ዉስጥ መኖር መጀመሬ ለክርስትና ሕይወቴ ማደግ ትልቅ አስተዋጸኦ አድርጎልኛል። መጀመሪያ ወደ አሜሪካ ስሄድ የተሸኘሁት ከዚያው ግቢ ነበር።

ከዚህቅርበትየተነሳአሜሪካተማሪበነበርሁበትዘመንየሜኖናይትሚሲዮናውያን በደብዳቤ ይከታተሉኝ ነበር፡፡ ከቤተሰባቸውና ከመጡበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋርም እንድገናኝ ያደርጉ ነበር፡፡ በአሜሪካ የመጀመሪያዎቹን ስድስት ወራት የኖርኩት አብዛኛዎቹ ሚሲዮናውያን ከመጡበት ለላንካስተር ቅርብ እኖር ስለነበር በዚያ የሜኖናይት ቤተ ክርስቲያኖች እየዞርሁ ምስክርነቴን እሰጥ ነበር። የሄድኩት የውኃ ጥምቀት ከወሰድሁ ከስድስት ወር በኋላ መሆኑንም





እገልጽ ነበር። በምስክርነቴ "የላካችኋቸው ሚሲዮናውያን ፍሬ ነኝ፤ እነዚህን ሚሲዮናውያን ስለ ላካችኋቸው በራሴና በኢትዮጵያ ስም አመሰግናለሁ" ስላቸው በጣም ደስ ይላቸው ነበር፡፡ ይህ ግንኙነትና በየቤተ ክርስቲያኑ እየዞርሁ አደርግ የነበረው አጫጭር ንግግሮች በጣም እንደ ጠቀመኝ አገምታለሁ፡፡ ቢያንስ በሰዎች ፊት ቆሞ የመናገር ድፍረትና ልምምድም ሰጥቶኛል፡፡ በአሜሪካ ሆኜ ከሜኖናይቶች ጋር የነበረኝ ግንኙነት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሼም ቀጥሏል፡፡ ተግባረ ዕድ ት/ቤት በማስተምርበት ጊዜ በመርሃ እውራን ት/ቤት ለሚደረገው አምልኮ ተሳታፊ ብቻ ሳልሆን ከመሪዎቹ አንዱ ነበርኩ፡፡ ደግሜ በ1952 ዓ ም መጨረሻ ወደ አሜሪካ ስሄድም ግንኙነቱ እንደገና ተጠናከሯል።

በ1951 ዓ ም ከየሚስዮኑ ጣቢያዎች የተውጣጣን (እኔና ሌሎችም ከአዲስ አበባ) ተሰብስበን ነበር፡፡ (ያ ስብሰባ እንደ መጀመሪያው የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መማከርት ጉባኤ ይቆጠራል፡፡) ለቤተ ክርስቲያናችን ስም የተጠቆመውና የእምነት እንቀጾቻችንም መጻፍ እንዳለብን የተረዳነው ያኔ ነበር። ስንጀምር የላንካስተር ሜኖናይት ኮንፈረንስ (Lancaster Mennonite Conferenc) የእምነት አንቀጽ ወደ አማርኛ እንዲተርጎም አደረግን፡፡ ተርጓሚው ንጉሤ አየለ (አሁን ዶ/ር) ነበር፡፡ በዚያ እምነት አንቀጽ ያከራከርን አንቀጽ ክርስቲያን ወደ ጦር ሜዳ አይሄድም የሚለው ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም ቢሆን ለወታደርነት የሚያስገድድ ህግ ስለ ሌለ ይህን አንቀጽ ማስቀመጡ እንደማይጠቅም ስለ ተገነዘብን አላስገባነውም።

## የሜኖናይትን ሚስዮን ሥራ መረከብ

መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሜኖናይት ሚሲዮን አገልግሎት ውጤት ናት። ይህ ሚስዮን የሚመራው ሳሉንጋ በምትባል በፔንሲልቫኒያ ግዛት (Pennsylvania State) ዉስጥ በምትግኝ ትንሽ ከተማ ዉስጥ ቢሮውን ባደረገ የሚስዮን ቦርድ ነው፡፡ ሚስዮኑ የሚታወቀዉ ት/ቤቶች፣ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች በማቋቋምና በማካሄድ ነው፡፡ "ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው

የሰማይ አባታችሁን እንዲያመሰግኑት የእናንተም ብርሃን በሰው ፊት ሁሉ ይብራ" የሚለውን መሠረት በማድረግ እነኚህን አገልግሎቶች በመስጠት ነበር የወንጌል ስራን የሚሰሩት። ጅማሬው ላይ እና በቀጣዩቹ ብዙ አመታት የሚሲዮኑ ዲሬክተር ዳንኤል ሴንሰኒንግ ነበሩ:: የሚስዮኑ ቦርድ ዋና ጸሐፊ ፖል ክሬይቢል የሚባለው በአመት አንዴ ወደ ኢትዮጵያ እየመጣ የሥራ አመራር ይሰጥ ነበር::

በ1955 ዓ.ም ባደረገው ጉብኝት "ከአሁን በኋላ የኢትዮጵያ አገልግሎት ከሳሉንጋ መመራት የለበትም፤ አመራሩ ከዚሁ ከኢትዮጵያ መሆን አለበት" በማለት አስታወቀ:: በየአመቱ የሚደረገው ጠቅላላ መማከርት ጉባኤ አመራሩን መረከብ አለበት ማለቱ ነበር:: ይህን እቅዳቸውንም በሰነድ (MEMORANDUM OF UNDERSTANDING) ላይ አስቀመጡ:: ሰነዱ በአጭሩ:- የሚሲዮኑ ቦርድ ለሚካሄዱት አገልግሎቶች ምን ያህል ሚስዮናውያንን እንደሚመደብ፤ ስነዚህ ሚስዮናውያን አበልና ኢትዮጵያ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን በርዱ እንደሚሰጥ፤ መኖሪያ ቤት ግን ቤተ ክርስቲያን መስጠት እንደሚገባት ያስቀመጠ ነበር። ለአግልግሎቶቹ ሥራ ማስኬጃ በአመት 100,000.00 ብር እንደሚመድብ፣ ቤተ ክርስቲያን በዚያ ላይ የተቻላትን እንድትጨምር:: ሥራው የሚመራው ስምንት አባላት ባሉት የሥራ አመራር ኮሚቴ እንዲሆን፣ አባላቱም አምስት ኢትዮጵያውያንና ሶስት ሚስዮናውያን እንዲሆኑ የሚያመለክት ነበር::

በወቅቱ ለኛ በግልጽ አይንገሩን እንጂ የሚስዮኑ ዓላማ ኃላፊነቱን በሙሉ ወደ ኢትዮጵያውያን ቀስ በቀስ፣ ደረጃ በደረጃ ለማስተላለፍና ቤተክርድስቲያን ለማቋቋም ነበር:: የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዋና ኃላፊነት የሚስዮኖች የስራ ቦታ መመደብ፤ ከኢትዮጵያ የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን መቅጠር፤ ከየአገልግሎት የሚገኙትንና ከአሜሪካ የሚሰጠዉን ገንዘብና አጥቢያዎች የሚያዋጡትን ማስተዳደር፤ ለጠቅላላ መማከርት ጉባኤና ለሚስዮኑ ቦርድ ሪፖርት ማቅረብ ነበር::





አንደኛ ደረጃ:- 1955 ዓ.ም

የሚስዮኑ ቦርድ ከሶስቱ ሚስዮናውያን (ሲንስኒንግ፣ ዌንገር፣ ጊንግሪክ) ሊቀ መንበርና አቃቤ ነዋይ መደበ:: ቤተ ክርስቲያን ከአምስቱ ኢትዮጵያውያን አንዱን ጸሐፊ አድርጋ እንድትመርጥ ተደረገ:: በዚህም መሠረት:-

1ኛ. ዳንኤል ሴንሰኒንግ:- ሊቀ መንበር፤

2ኛ. ፖል ጊንግሪክ:- አቃቤ ነዋይ፤

3ኛ. በየነ ሙላቱ :- ጸሐፊ እንዲሆኑ ተወሰነ::

ሁለተኛ ደረጃ:- 1956 ዓ.ም

በዚህ አመት በነበረው ጉብኝት ትንሽ ለውጥ እናድርግ ተባለ። ሦስቱ ሚሽዮናውያን•በኮሚቴው አባልነታቸውን ይቀጥላሉ፤ ሆኖም ከሦስቱ ማን ሊቀ መንበር፣ ማን አቃቤ ንዋይ እንደሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ይወስኑ ተባለ:: ትንሽ ስልጣን ብጤ ለቤተ ክርስቲያን ተሰጠ ማለት ነው:: ቼስተር ዌንገር ሊቀ ምንበር ሲሆኑ፣ ፓል ጊንግሪክ አቃቤ ነዋይ በመሆን ቀጠሉ::

ጎን ለጎን የቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ በሚገባ እንዲዘጋጅ ትልቅ ጥረት እየተደረገ ነበር:: በመንግስትም ለመታወቅ መሟላት ያለበትን ቅድመ ሆኔታ ስንጠይቅ የምንመዘገበው እንደ ማሕበር እንደ ሆነና በምዝገባው ማመልከቻ ላይ የጊዜው የማሕበሩ ሹማምንት ማን ማን እንደሆኑ መገለጽ እንዳለበት ተረዳን:: የጊዜዎቹ ሹማምንቶች ከፊሎቹ የውጭ አገር ዜጎች በመሆናቸው ችግር እንደሚፈጥርብን ተገነዘብን::

### ሦስተኛ ደረጃ፡- 1957 ዓ.ም

በመስከርም ወር 1957 ዓ.ም በተደረገው የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ የመካከርት ጉባኤ (ጠመጉ) የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል ሆኜ ተመረጥኹ። በዚህ አመት ፖል ክሬይቢል ሲመጣ ሰምዝገባ አሁን ብንሄድ ከሹማምንቱ አሜሪካን ስላሉበት ችግር እንደሚገጥመን ገለጽንስት፡፡ እርሱም "ይህ ምንም ማለት አይደለም፤ ሕጉ በሚሰው መሠረት ኢትዮጵያውያን ሹማምንት ይመረጡ፤ ሚስዮናውያን ሹማምንት ሥራውን እየሠሩ ረዳት ይባሉ፤ ሥራውን እነርሱ መሥራት ይቀጥሉ" ስላስን ሃሳቡን ተቀበልንና ከዚህ እንደሚከተሰው ጠመጉ ወሰነ።

ሊቀ መንበር፡- ሚሊዮን በለጠ፤ ረዳቱ፡- ቼስተር ዌንገር፡፡

አቃቤ ነዋይ፡- ሙሉነህ ባቾሬ፤ ረዳቱ ፖል ጊንግሪክ፡፡

ጸሐፊ፡- በየነ ሙሳቱ፡፡

ሚስተር ዌንገር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተማሩኝ ሰው ናቸው፡፡ የእርሳቸው የእኔ ረዳት መባላቸው አልተዋጠልኝም፡፡ ሆኖም ለስሙ እንጂ ሥራውን ይቀጥላሉ በማለት ነገሩን ተቀበልሁት፡፡ ከምርጫ በኋላ በመጀመሪያው ስብሰባችን ስብሰባውን እንዲመሩ ስጠብቃቸው፣ በል ቀጥል ካስፈለገ እለሁ አሉኝ፡፡ አጥብቄ ብጠይቃቸውም፣ ስብሰባውን እንድመራ አጥብቀው ገፋፉኝ፡፡

አሜሪካ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ስለ ዘመናዊ ስብሰባ አመራርና ሂደት አንድ ሥልጠና ወስጄ፣ በክፍል ውስጥም ጥቂት ተሰማምጄ ነበር፡፡ የሚስተር ዌንገርንና የሚስተር ሴንስኒንግ የጉባዔ አመራረንም ተመልክቼአለሁ፡፡ በእርሳቸው ማደፋፈር መምራቱን በድፍረት ተቀብዬ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የመሠረት ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሊቀ መንበርነትን በስምም በሥራም ተቀዳጀሁ፡፡ ይህ ሹመት የብዙ አገራዊ፣ አሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎችን እንድሳተፍ አብቅቶኛል።





ከይቅርታ ጋር አንባቢዬ ወደ ኋላ ልመስሰውና፣ የዓፄ ገላውዴዮስ ት/ቤት ዲሬክተር በነበርኩበት ወቅት በናዝሬት መሠረተ ክርስቶስ እንዳገለግል የመጀመሪያው የመሠረተ ክርስቶስ መጋቢ ሆኜ መካኔን ከዚህ በፊት ገልጫለሁ፡፡ ምን ተብዬ ልጠራ እንደሚገባኝም መጠነኛ ውይይት አድርጌ ነበር፤ በእንግሊዝኛው ሬቨረንድ (Reverend) ነው የምባለው፤ የዚህ ቃል ትርጉም ወይም አባባል በኢትዮጵያ ምን መሆን አለበት? ብለን አሰብን፡፡ አንድ ቀን ሚስዮናዊው ናታን ሄጊ እንዲህ ያለ ሰው ምን ይባላል? ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ጥያቄያቸውን በምሣሌ ሲያብራሩ፤ "ወደ አንድ ድግስ ቤት ብትሄድ፣ ሰምግቡ እንድታመሰግን ወይም ምግቡን እንድትባርክ ስትጋበዝ አቶ ሚሊዮን ተብሰህ ልትጠራ አይገባህም" አሉኝ፡፡ "እንደዚህ ያስ ሹመትን ተራው ሰው ምን ብሎ ነው የሚረዳው?" አለኝ፤ አስብሁ፤ "ቄስ ነው" አልኩት፡፡ "ታዲያ ሰምን ቄስ አትባልም?" ሲል ጠየቁኝ፡፡ በዚሁ ተስማማን አገር ውስጥ በማዕረጉ ሳልጠቀም ነበር ወደ ናይሮቢ የሄድኩት፡፡ ናይሮቢ በነበርኩበት ጊዜ የመታወቂያ ካርድ በእንግሊዝኛው ሬቨረንድ ሚሊዮን በለጠ (Rev. Million Belete) ብዬ አሳተምኩ፡፡ ቋንቋችንን ሰማስተዋወቅም በአማርኛም ቄስ ሚሊዮን በለጠ የሚል ካርድ አሳትሜ ነበር።

### አራተኛ ደረጃ፡- ለቤተ ክርስቲያናችን ስም ማውጣት

1957 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያናችን ስም የተመረጠበት አመት ነበር፡፡ በመጀመሪያው ጉባዔ (1951 ዓ.ም) "መሠረተ ክርስቶስ (Christ Foundation Church)" የሚለውን ስም ንጉሤ አየለ ጠቁሞ ነበር። ከሜኖናይት ጋር ግንኙነታችንን የሚገልጽ ስያሜ ቢሆን የሚሻል መሆኑንም የጠቆሙ ነበሩ፡፡ "መሠረተ ክርስቶስ - ሜኖናይት" እንዱ የቀረበው አማራጭ ነበር፡፡ የወቅቱ ሊቀመንበር እኔ ስለነበርኩ እያንዳንዱን ሂደት በሚገባ አስታውሳለሁ፡፡ ዝርዝሩን ማተት ግን እንባቢን ማታከት ይሆንብኛልና ልተወው፡፡

በዚያን አመት በመንግሥት ዘንድ እንድንታወቅ ማመልከቻ ስማስገባት ተወሰነ። የመጀመሪያ አጀንዳችንን ስከፍት "የምንታወቅበት ስም ያስፈልገናል፤ ተጠቁሞ

ሲንገዋሰል የቆየ ስም አስ፤ ሌላም አዲስ ስም ካስ ይጠቆምና እንወስን" ብዬ ጠየቅኹ፡፡ የተሰነዘሩትን ስያሜዎች በሰሌዳ ላይ ጻፍኩ፡፡

መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን/ማሕበር፤

መሠረተ ክርስቶስ (ሜኖናይት) ቤተ ክርስቲያን/ማሕበር፤

ቀራንዮ ቤተ ክርስቲያን/ማሕበር፤

ቀራንዮ ሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን/ማሕበር፤

ቀራንዮን የጠቆምኩት እኔ ነበርኹ፡፡ አሁን የማላስታውሳቸውና ሌሎች የቀረቡ ስያሜዎችም ነበሩ፡፡ በድምፅ ብልጫ የቤተ ክርስቲያናችን ስም መሠረተ ክርስቶስ ይሆን ዘንድ ወሰንን፡፡ በተጨማሪም በዘያ ጉባዔ ነበር፣ ማሕበር ከመባል ይልቅ ቤተ ክርስቲያን መሆናችንን የወሰነው፡፡

ያኔ ሕጋዊ እውቅና ለማግኘት ማመልከቻ የሚቀርበው "ጸጥታ መሥሪያ ቤት" ለሚባለው ተቋም ነበር፡፡ ማመልቻችንን ከአምነት መግለጫችን ጋር አባሪ አድርገን አስገባን፡፡ ከአንድ ወር በኋላ መሥሪያ ቤቱ ጠራኝ፡፡ ከአምነት መግለጫችን አንዱ አንቀጽ "በምስጥራዊ ስምምነት አናምንም" የሚል ነበር፡፡ ባለሥልጣኑ፡- "እንዲህ ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው ብለው ጠየቁኝ"፡፡ በቤተ ክርስትያናችን ውስጥ ምንም ምስጢር አሠራር የለም፤ ሁሉ ነገር በግልጽ መደረግ አለበት ማለታችን ነው" አልኳቸው፡፡ አሁን ትዝ የማይሰኝን ሌላ ጥያቄ አንስተው ማብራራቴን አስታውሳለሁ፡፡ "ምላሻችንን እንስታውቃችኋለን" በማለት አሰናበቱኝ፡፡ ደርግ ስልጣን እስኪይዝ ድረስ ምንም መልስ አልተሰጠንም ነበር።

## በዓለም ሜኖናይት ኮንፍረንስ ላይ ተሳትፎዬ

(Mennonite World Conference
Africa Mennonite and Brothern in Christ Fellowship)

በ1957 ዓ.ም የአፍሪቃ ሜኖናይቶች መሪዎች ስብሰባ ላይ ተገኝቼ ነበር፡፡





ስብሰባው የተደረገው ዚምባቡዌ (የያኔዋ ደቡብ ሮዴሺያ) ላይ ሲሆን ተካፋዮቹ ከጋና፣ ኮንጎ፣ ኢትዮጵያ፣ ሱማሊያ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ዛምቢያና ከዛው ከሮዶሺያ የተውጣጡ ነበሩ፡፡ በስብሰባው የተገኘነው ሚስዮናውያንና አፍሪቃውያን ነበርን፡፡ እንድንተዋወቅ ስብሰባውን ያደራጀልን ኤም.ሲ.ሲ..(Mennonite Central Committee) ነበር፡፡ ከኢትዮጵያ የሄድነው ኪሮስ ቢሆን፣ በየነ ሙላቱ፣ ሽምሱዲን አብዶ፣ ሚስርተር ጊንግሪክ፣ ናታን ሄጊና እኔ ነበርን፡፡

ስብሰባውን በሊቀ መንበርነት የሚመራው አፍሪቃዊ እንዲሆን ታሰበና እኔ እንድመራ ተደረገ፡፡ ያኔ ነበር አፍሪቃ ሜኖናይት ኤንድ ብራዘረን ኢን ክራይስት ፌሎሺፕ (Africa Mennonite and Brothern in Christ Fellowship) በሚል የአፍሪካን ድርጅት የመሰረትነው።

በዚያ ስብሰባ ላይ በአሰም ሜኖናይት ኮንፈረንስ ላይ አፍሪቃ እንድትወከል ጥያቄ ቀርቦ ስለ ነበር እኔ ተወከዬ በአምስተርዳሙ በሚደረገው ቀጣይ ስብሰባ እንድሄድ ተወሰነ፡፡ ያ ስብሰባ ከሁሰት አመት በኋላ ስለሚደረገው የ1967 (እኤአ) አለም አቀፍ ስብሰባ ዝግጅት ለማድረግ ነበር። እዚያ ደግሞ የሥራ አመራር ኮሚቲ ማቋቋም ስላስፈለገ ከአፍሪቃ የሜኖናይት ወርልድ ኮንፈረንስ ም/ፕሬዚዳንት የሚል ሹመት ሰጥተውኝ ማገልገል ጀመርኹ፡፡ አፍሪቃን መወከል ለእኔ ትልቅ ክብር ነበር፡፡



እንድወክላቸው ወደ ሜኖናይት አለማቀፍ ኮንፈረንስ የላኩኝ የአፍሪቃ ሜኖናይት እና ብራዝረን ኢንክራይስት ፌሎምሺፕ

በ1967 ዓ.ም (እ.አ.አ )ስብሰባው በአምስተርዳም ተካሄደ:: እኔም ኢትዮጵያንና አፍሪቃንም በመወከል ከመላው አለም ከመጡ ሜኖናይቶች ጋር ተካፋይ ሆንሁ:: ጥቂት ሌሎች አፍሪቃውያንም ተካፍለው ነበር። ያን ስብሰባ በጸሎት የከፈትኩት እኔ ነበርኹ፤ ስብሰባው በስርአት እንዲሄድ ከሚያደርጉት መሪዎች መቆጠሬን ሳስበው ያስገርመኛል::

ያ ስብሰባ እንዳለቀ የሚቀጥለው ስባተኛ ስብሰባ መቼና የት ይሁን የሚለውን መወሰን ነበረብን:: በ1972 (እ.አ.አ) በብራዚል እንዲሆን ወሰነን ዝግጅቶቹን ለሥራ አመራር ኮሚቴው ሰጥተን ተለያየን:: የዚህ ድርጅት ሥራ አመራር ኮሚቴ  አባልነቴንም እንድቀጥል ተጠየቅሁ:: ሌሎቹ ከአሜሪካ፣ ሆላንድ፣ ሕንድ፣ ኢንዶኒዢያ፣ ብራዚል፣ ጀርመን፣ የተውጣጡ ነበር:: የብራዚሉ ስብሰባ እስኪደረግ ድረስ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቲው በልዩ ልዩ አገሮች (ኢትዮጵያ አሜሪካ፣ ሕንድ፣ ኢንዶኒዢያ፣ ብራዚል) በየአመቱ በመሰብሰብ አዘጋጀን:: በዚህ ኮሚቴ ላይ ማገልገሌ ብዙ የአመራር ትምህርቶችን ከመቅሰሜም በላይ ብዙ አገሮችን አንዳይ ዕድል ሰጥቶኝ ነበር::

በ1972 በብራዚል ከተደረገው ስብሰባ በኋላ ስምንተኛውን ስብሰባ እንዲዘጋጅ በ1973 በስዊዘርላንድ ልዩ ስብሰባ ተደረገ:: ያ ጉባኤ  የሰጠኝ ኃላፊነት ታላቅና ያላሰብኩት ነበር:: በስብሰባው ላይ ከመላው አለም የተሰበሰብን ሃያ ያህል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበርን:: የስብሰባው ሁለት ዋና ዋና አጀንዳዎች ፕሬዚደንትና ዋና ጸሐፊ መምረጥ ነበር::

የሜኖናይት አለም አቀፍ ስብሰባ ከተጀመረ ጀምሮ የነበሩት ፕሬዚዳንቶች ከአሜሪካ ወይም አውሮፓ ስለነበሩ ዛሬ የሚመረጠው ፕሬዚደንት ከሶስተኛ አለም መሆን ይገባዋል ተባለ:: ጎኔ ተቀምጦ የነበረ የማዳ የሚባል ጃፓናዊ ተጠቆመ:: የማዳ አሻፈረኝ አልሆንም አለ:: እንዲቀበል እኔም የበኩሌን ጉትጎት አደረኩት:: የማዳ ግን በአምቢታው ጸና። ሊቀ መንበራችን የማዳን ሰጎተጉተው ሰምተው ስለነበር "ለሻይ እንውጣ፣ በነገሩም እያሰብን እንቆይ፤ ለሚሊዮንም ከየማዳ ጋር ጊዜ እንስጠው" አሉና ለሻይ ወጣን።





ለሻይ ስንወጣ  እንደገና የማዳን ወተወትኩት::  "እነኚህ አውሮፓውያን ይህ ድርጅት እንደሌሎች የአውሮፓውያን አለመሆኑን በተግባር አንድንገልጽ ይፈልጋሉ፤ ስለዚህ መቀበል አለብህ" አልኩት፤ አሻፈረኝ አለ::  ከሻይ መልስ የማዳን "ምን ትላለህ" ቢሉት  "አልሆንም" አለ። ከዚያ በኋላ አንዱ  መግለጫ ብጤ ሰጠና ሚሊዮን ፕሬዚደንት እንዲሆን ሃሳብ አቀርባለሁ አለ::  እኔም በበኩሌ "እኔ ዶክተር ዎልትነርን  መተካት አልችልም፤ የማይመስል ነገር ነው፤ ለዚህ ብቁ አይደለሁም" አልኩ:: አንዱ ሲመልስ "የማዳንን ምን ነበር ስትለው የነበረው? እንዴት አልችልም ትላለህ?" አለኝ:: ሌሎችም ተመሳሳይ አስተያየቶች ሰጡ "ለየማዳ ያልከውን  ምክር ፈጽም በማለት ገፋፉኝ" ሳልወድ በግድ እሺ አልኹ:: እንግዲህ የሚኛው ባላገር የሜኖናይት ዎርልድ ኮንፈረንስ ፕሬዚደንት ሆነ ማለትም አይደል! የጌታ ሥራ ይገርመኛል!



የሜኖናይት አለማቀፍ ኮንፍረንስ ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ

ይህን የፕሬዝዳንትነት ባርኔጣ ደፍቼ ብዙ አገሮች አይቼአለሁ::  ከሄድኩባቸው አገሮች አንዱ ሩስያ ነበር:: በሩስያ ያሉት ሜኖናይቶች ከጀርመን ወይም ከአሜሪካ ሳይሆን ከአፍሪቃ የመጣ ጥቁር ሜኖናይት በማየታቸው ተገረሙ::

ቡተጨማሪም ኢትያጵያ በጊዜው የነበረቺው በኮሙኒስት ስርአት (ደርግ) ሥር ስለነበር ከኢትዮጵያ መምጣቴ ልዩ ትርጉም ሰጣቸው።



በሞስኮ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን አጭቅ ብሎ ለተቀመጠ ህዝብ መልእክት ሳቀርብ



በዊቺታ (አሜሪካ) በተደረገው የሜኖናይት አለማቀፍ ኮንፍረንስ ላይ ከተገኙ መስከባውያን ጋር



አሜሪካዊው መርቪን ሄይን እና ኢትዩጵያዊው ሚሊዮን በሜኖናይት አለማቀፉ ኮንፍረንስ ላይ ለመገኘት የመጡትን ሩሲያውያን ስንቀበል





እኔ ፕሬዚደንት ሆኜ ስሾም ለረጂም ጊዜ የማውቀው የቀድሞው የእኛ ሚስዮን ቦርድ ዋና ጸሐፊ የነበረው ፖል ክሬይቢል ለሜኖናይት ዎርልድ ኮንፈረንስ ሥራ አስፈጻሚ ዋና ጸሐፊ(Executive Secretary) ሆኖ ተሾመ:: ይህ ለእኔ ተጨማሪ ድፍረት ሰጠኝ:: ፖል ግሩም ሥራ አቀነባባሪ ነበር:: የስምንተኛውን ጉባኤም ሥራ አመራር ኮሚቴው በልዩ ልዩ ቦታዎች በመሰብሰብ አዘጋጅቶ ስምንተኛው የሜኖናይት ዎርልድ ኮንፈረንስ ስብሰባ በአሜሪካ ዊቺታ ከተማ በሐምሌ ወር 1970 ዓ.ም ተደረገ:: ያን ስብሰባ ከመራሁ በኋላ ከሜኖናይት ዎርልድ ኮንፈረንስ ተሰናበትሁ። በአፍሪቃው ድርጅታችን ላይ ግን ማገልገሌን ቀጠልሁ:: ይህንን ሁሉ የማገልገል እድልና ታላቅ ክብር ያገኘሁት በመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በነበረኝ ተላትፎ ምክንያት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን አመሰግንዋለሁ።

## ምዕራፍ 9

# ከመንግሥት ቤት መለያየት፤

## መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር

ለአጭር ጊዜም ቢሆን ናዝሬት ከተማ በሚገኘው አጼ ገላውዲዮስ ት/ቤት በዲሬክተርነት ማገልገሌ ይታወሳል፡፡ እዛ በነበርኩበት ጊዜ ጆ. ናይት የሚባለው የመጽሀፍ ቅዱስ ማህበር ወኪል ወደ ናዝሬት ቢሮዬ መጥቶ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ሥራ አመራር እንዲህ ብሎ ገለፆልኝ ነበር። የእንግሊዝና የውጭ አገሮች መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር (British and Foreign Bible Society በምህፃረ ቃል BFBS) ለዘመናት ቅዱሳት መጻሕፍትን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያቀርብ ቆይቷል። በመላው አለም የሚገኙ የተደራጁ ብሔራዊ ማሕበሮች በኅብረት ለመሥራት ስለ ወሰኑ United Bible Societies በአጭሩ UBS በሚል ስም ተደራጅተዋል፡፡ የየአገራቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ሥራ እነኚህ የተደራጁ ማሕበሮች ተከፋፍለዋል። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያውን ሥራ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ተረከቧል፡፡

ከአሁን በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ስራ በየአገሩ የአማካሪ ቦርድ ተሰይሞ በእነሱ ምክር መመራት እንደ አለበት ስለታመነበት ከየአብያተ ክርስቲያኑ የተውጣጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አማካሪ ቦርድ ተቋቋመ፡፡ በዚህ አማካሪ ቦርድ እንዳገለግል ተጠቁመሃል አለኝ፡፡ በዚህ ቦርድ ላይ እንዲያገለግሉ የተሰየሙትና የተቀበሉትም፣ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ክቡር አቶ አበበ ረታ፣ ሊቀ ሥልጣናት ሐብተ ማርያም (በዚያን ጊዜ የቅድስተ ሥላሴ ካቴድራል ኃላፊ) አሁን አቡነ መልከጼዲ - - - ዶ/ር ጌታቸው ኃይሌ፣ ከመካነ ኢሱስ ክቡር አቶ አማኑዔል አብርሃምና ዶር አማኑዔል ገ/ሥላሴ፤ ከቃለ ሕይወት አቶ ሐዋዝ





ወልደ ሚካኤል፤ ከሚስዮኖች ሚ/ር ሚካኤል ብሌር የሥራዊት ክርስቶስ ማሕበር (B.C.M.S. missionary) ነበሩ። ኋላ ላይ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የታከሉ ነበሩ፡፡ በዚህ ታላቅ ሥራ ከእነዚህ ታላላቅ ሰዎች ጋር መጠመዱን እንደታላቅ ክብርና የአገልግሎት እድልም ስለነበር ጥቆማውን በአሺታ ተቀበልኩት፡፡

በዚህ አማካሪ ቦርድ ስብሰባ ላይ ሳልገኝ ናዝሬትን ለቅቄ ወደ ባሕር ዳር ተመለስኩ፡፡ ቢሆንም የቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች ይላኩልኝ ነበር፡፡ ቦርዱ እንደ ዋና ሥራው አድርጎ የነደፈው ብሔራዊ ማሕበር ማቋቋምና ብሔራዊ ጠቅላይ ጸሐፊ መመደብ ነበር። ጸሐፊው እራሱ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብና መልእክቱ ለሌሎች እንዲደርስ የሚፈልግ ሰው መሆን እንደሚገባ ቦርዱ ወስኖ ነበር።

ዋና ጸሐፊ የሚሆን ሰው ሲያፈላልጉ እኔ ተጠቆምኩና ሚ/ር ብሌር እንዲያነጋግረኝ ወሰኑ። ሚ/ር ብሌር ሲጠይቀኝ ገረመኝ፤ ተደነቅሁም፡፡

"እኔ የሰለጠንኩት የኤሌትሪክ ቴክኖሎጂ ነው፤ ትምህርተ መለኮትም ሆነ የንግድ ሥራ ትምህርት የለኝም፡፡ ለዚህ ሥራ ብቁ አይደለሁም" በማለት መለስኩለት፡፡ ተስፋ ሳይቆርጥ አብዝቶ ገፋፋኝ እንዲህ ሲል፡-

"የተጠቆምከው ዋና ምክንያት ለወንጌል ሥርጭት ባለህ አቋም ነው፤ ያንተ ሥራ የአስተዳደር ሥራ ስለሆነ ፖሊቴክንክን ማስተዳደር ከቻልክ ይህንንም ትችላለህ ብለን ገምተናል፤ የንግዱን ጎን (መጽሐፍ የመሸጥና ሂሳብ መዝገብ ጉዳይ) በተመለከተ ረዳት ይቀጠርልሃል"፡፡

ማይክልን አውቀዋለሁ፤ ብዙ ከተነጋገርን በኋላ ልጸልይበት፣ ከባለቤቴም ጋር ልምከር ብዬ ተለያየን። በዚያው ዕለት የሚስዮናችን ጀማሪና ዲሬክተር ጋር ለመመካከር አሰብኩ። እሳቸውም ምራቃቸውን የዋጡ፣ አዋቂና ስለ ክርስቶስ ብዙ ያስተማሩኝ ሚ/ር ሲንስኒንግ ነበሩ፡፡ ሄጄም አማከርኳቸው፡፡ በጉዳዩ ውስጥ እርሳቸውም ስለ ነበሩበት ከኛ ሚስዮን/ቤተ ክርስቲያን ማን ይጠቆም ሲባልም እኔን የጠቆሙት እርሳቸው ነበሩ፡፡

የኔ ፍላጎት ክቤተ ክርስቲያን ውጭ በመስራት ጌታን ማገልገል ነው፤ 'ሚሊዮን ገንዘብ ስለሚያገኝ ወይም ስለሚከፈለው ነው የሚሰብከው' እንድባል እንደማልፈልግ ስነግራቸው:-

"ታዲያ የመጽሐፍ ቅዱስን ማሕበር ክርስቶስን የማያውቅ የዓለም ሰው እንዲሆን ነው የምታስበው?" በማለት በጥያቄ ወጋ አደረጉኝ፡፡

ሙያዬን እወደዋለሁ፤ በሠለጠንኩበት ሙያ በቀጥታ እየሠራሁ ባይሆንም ለኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች የሰው ኃይል የሚያሠለጥን ተቋም ዲሬክተር በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡፡ ስለዚህም ከሙያዬ መራቁ ከበደኝ፡፡

በሌላ በኩል ወደ አስተዳደር ሥራ ገብቻለሁ፤ የታጋበዝኩት ለእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ የተቋቋመ ማሕበር አስተዳዳሪ እንድሆን ነው፡፡ መቅደም ያለበት የቱ ነው? 'የእግዚአብሔር ፈቃድስ የቱ ነው?' በማለት አሰላሰልኩ፡፡ ሚዛኑ ጥያቄውን ወደ መቀበሉ አዘነበለ፤ ግደይን ሳማከራት የእሷም ልብ ወደ መቀበሉ አዘነበለ፡፡ ልባችን አንድ ሆኖ አዲሱን ጥሪ ለመቀበል ወሰንን፡፡ በወቅቱ ከፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት የመጀመሪያዎቹን ምሩቃን በጃንሆይ አስመርቄ፣ ምሩቃኑንም በየኢንዱስትሪው ሥራ በማስያዝ ላይ ነበርኩ፡፡

የ1960 ዓ.ም የትምህርት ዘመን እንደ ተጀመረ የሥራ ስንብት ማመልከቻ አስገባኩ፡፡ የቅርብ አለቃዬ የነበሩት አቶ ተድላ ዘዮሐንስ ከብዙ ማቅማማትና ውይይት በኋላ ፈቀዱልኝ፡፡ በዚሁ መሠረት ሥራዬን ለምክትሌ ማስረከብ እንድጀምርና የመልቀቂያ ደብዳቤው የሚፈረመው ግን በም/ምኒስትሩ በአቶ ሚሊዮን ነቅንቅ ወይም በምኒስትሩ በአቶ አካለወልድ እንደሚሆን ነግረውኝ ወደ ባሕር ዳር ተመለስኩ፡፡

ምክትሌ በየነ በቀለም ሆነ መምህራት ሥራውን ለመልቀቅ በመወሰኔ አዘኑ፡፡ በትምህርት ቤቱ ያሉት ወንጌላውያን ተማሪዎችም (እነ ካሣ አጋፋሪ) የበለጠውን አዘኑ፡፡ ሥራዬን ለምክትሌ ለአቶ በየነ በቀለ አስረክቤ በህዳር ወር መጀመሪያ ላይ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ወደ ት/ምኒስቴር የስንብት ወረቀቴን ለመቀበል ሄድኩ።





የስንብት ደብዳቤዬን ይሰጡኝ ይሆን አይሰጡኝ? የሚል የፍርሃትና የምኞት ድብልቅ ስሜት ነበረኝ፡፡፤ ት/ሚኒስቴር እንደ ደረስኩ ምክትል ምኒስትሩ አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ ሊያነጋግሩኝ እንደሚፈልጉ ስለ ተነገረኝ ወደ ቢሮአቸው ሄድኩ።

"ለምንድነው የምትተወን?" አሉኝ - ኮስተር ብለው፡፡ አቶ ሚሊዮን ተክለ ሰውነታቸው ግዙፍ፣ አስፈሪ ግርማ ሞገሥ ያላቸው አለቃ ነበሩ፡፡ የምለቅበትን ምክንያት ሳስረዳቸው በጥሞና ከሰሙኝ በኋላ፣ አሁንም በቁጣ መልክ:-

"ታገኟታላችሁ!" ሲሉኝ:-

"ምን ማለትዎ ነው ጌታዬ?" በማለት ጠየቅኋቸው፡፡

"ወጣቱን ማን ያስተምረው ብላችሁ ነው እየተዋችሁት ወደየጥቅማችሁ (ኢንዱስትሪው) የምትሄዱት?" ብለው - በቀሪው ገጽ ላይ ምልክት

አድርገው፣ "ያውልህ ምኒስትሩ ይፈርሙልህ" በማለት አሰናበቱኝ፡፡

ምኒስትሩ አቶ አካለወርቅ ሐብተወልድ አርቶዶክስ አለመሆኔን ብቻ ሳይሆን በሥራ ጉዳይ በተመደብኩባቸው ቦታዎች ሁሉ የማደርገውን ወንጌላዊ ጅምሮች የሰሙ ይመስለኛል፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት ግርማዊነታቸው ለፖሊቴክኒክ ምሩቃን ስነስርአት መጥተው በነበርበት ወቅት ወደ ግቢ ሲገቡ አብሬያቸው መቀበሌንና፤ እርሳቸውም ስግርማዊነታቸው የት/ቤቱ ዲሬክተር መሆኔን ማስተዋወቃቸውን ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ያውቃሉ፡፡ በማግሥቱ ስመስስ ደብዳቤው ተፈርሞ ጠበቀኝ። ደብዳቤው በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ፣ በመቀሌና ባሕር ዳር በጠቅላላው ለዘጠኝ ዓመት ማገልገሌን ይጠቅሳል፤ ይህ ሁሉ ስጡረታ ይጠቅማል ተብሎ የተካተተ መሆኑ ነበር፡፡

ክአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር Executive Secretary for Bible Society in Ethiopia የሚል የሹመት ደብዳቤ ቀደም ብሎ ደርሶኝ ስለነበር በወቅቱ የኢንተሪም ኤክዘኪውቲቭ (Interim Executive Secretary) ለነበረው ለሚስተር ኸርብ ካስለር የስንብት ወረቀቴን ማግኘቴን ስነግረው በጣም ደስ አለው፡፡ እንግዲህ ከዛሬ November 15, 1967 (ህዳር 6/1960 ዓ.ም) ጀምሮ

ኢትዮጵያዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ጸሐፊ አገኘች ብሎ ፈነደቀ፡፡

እቃችንን የት/ቤቱ የጭነት መኪና ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ እንዲያጓጉዝልን አመቻችቻለሁ፤ ቤተሰቤ በአውሮፕላን መጥቶ ማረፊያችንን መሠረተ ክርስቶስ እንግዳ ማረፊያ አደረግን፡፡ በቀ.ኃ.ሥ. ጎዳና ፒያሳ ያለው ሕንፃ ዓላማው ለመሥሪያ ቤትነትና ለኃላፊው መኖሪያ ቢሆንም ፒያሳ መሐል መኖሩን አልወደድኩትም። በዛ ፈንታ ያን አከራይተን ሌላ ቦታ መጠኑ ተመሳሳይ የሆነ ቤት እንድንከራይ ተስማማን፡፡ ግደይ እንደ መጣች የእንግዳ ቤቱ ኃላፊ ከነበረቺው ከሚስ ሣራ ረሽ ጋር ቤት መፈለግ ጀመሩ፡፡ ኸርብ ካስለር በሰጣቸው የኪራይ ገደብ ከቤተ ክርስቲያናችን አለፍ ብሎ ወደ ቦሌ በሚወስደው መንገድ ጥሩ ቪላ ቤት አገኙና የመጀመሪያ መኖሪያችንን እዛ አደረግን፡፡ (እዚያ ቤት ዉስጥ ሆነን ነበር ወንድሜን አሸብርን የዳርነውና ጎጆ ያስወጣነው፡፡ ጌድዮንና ሄኖክ ሚዜዎች (ሻማ ያዦች) ነበሩ)፡፡



የአሸብር ሚዜዎች

በመማከርት ጉባኤ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስገኝ ጥሪያቸውን በመቀበሌ አመሰግነው የሚከተለውን መመሪያ ሰጡኝ፦ (ሀ). ከሚ/ር ካስለር ስለ ማሕበሩ አሠራር እንድማር፤ (ለ). ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት ለማገልገል እንድዘጋጅ፤ (ሐ). ማሕበሩን ብሔራዊ ማሕበር እንዲሆን ጥረት እንዳደርግ ነበር፡፡

***

የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ዋና ዓላማ ቅዱሳት መጻሕፍት ሰዎች በሚገባቸው ቋንቋና ሊገዙ በሚችሉት ዋጋ ለሰዎች





ማቅረብ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሰ ማህበር እንዴት እንደ ተጀመረ የምትገልጽ ሜሪ ጆንስ የምትባል የአንዲት ልጅ ታሪክ ነበር፡፡ ይህ ታሪክ የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበሮች ሁሉ እናት የሆነቺው የእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (British and Foreign Bible Society) መቋቋም መነሻ የሆነ ነበር፡፡ ስለ አጀማመሩ ጥቂት ላካፍላችሁ፡፡

## የእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (BFBS) አጀማመር

ከደሃ ቤተሰብ የተወለደች በዌልስ የምትኖር ሜሪ ጆንስ የምትባል ልጅ ነበረች። ይህቺ ልጅ በሰንበት ት/ቤት የምትሰማቸውን አስደናቂ ታሪኮች የሚገኙበትን መጽሐፍ ቤተሰቦቿ እንዲግዙላት ጠየቀቻቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ መግገ ገንዘብ እንደ ሌላቸው ሲነግሯት ገንዘብ ለማጠራቀም ወሰነች፡፡ በስጦታ ባገኘቻቸው ላንቲሞች ላይ ልዩ ልዩ ነገሮችን በመሥራት አንድ አመት ያህል ገንዘብ አጠራቀመች፡፡

ሜሪ ጆንሰ ከአንድ 'አመት በኋላ ባጠራቀመችው ገንዘብ ወላጆቿ መጽሐፍ ቅዱሰ እንዲገዙላት ጠየቀቻቸው፡፡ "አዬ! ይሄ አይበቃም፤ መጽሐፍ ቅዱሰ በዚህ ገንዘብ መግዛት አይቻልም" አሏት፡፡ ተሰፋ ሳትቆርጥ ሰሰድሰት አመታት ሰፍታ ካጠራቀመች በኋላ መጽሐፍ ቅዱሰ መግዛት ብትፈልግ በዌልሰ ከተማ የሚሸጥላት ሰው አጣች፡፡ ሰታጠያይቅ አርባ አምሰት ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኝ ከተማ መጽሐፍ ቅዱሰ የሚሸጥ ሰው መኖሩን ሰማች። አንድ ቀን በጠዋት ተነሰታ በእግሯ ጉዞዋን ቀጠሰችና ወደ ምሽት ከተማዋ ዳር ደረሰች፡፡ አንድ ሰው አግኝታ የዚያን ነጋዴ አድራሻ ሰታጠያይቅ፣ ሠፈሩ ራቅ ብሎ እንደሚገኝ ነገራት፡፡ ሰዓቱ ሰለ መሸ እርሱ ቤት አድራ በማግሥቱ መሄድ እንደሚሻላት፣ እርሱም በማግሥቱ ወደ እዚያው ሰለሚሄድ አድራሻውን እንደሚያሳያት ነገራት፡፡ መስተንግዶውን ተቀብላ እዛው ሰው ቤት አደረች፡፡

ማታ ላይ በአንግድነት ካስተናገዳት ሰው ጋር መወያየት ጀመሩ:: ላለፉት ስድስት አመታት ገንዘብ እንዴት እንዳጠራቀመች፣ እስከ አሁን ድረስ ጎረቤት እየሄደች ያንዲት ሴትን መጽሐፍ ቅዱስ እያነበበች እንደ ቆየች ነገረቻው:: ሰውዬውም የሜሪ ጆንስን ጥረት አደነቀ:: ሜሪ በማግሥቱ የራሷ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚኖራት ስታስብ እንቅልፍ ሳይወስዳት አደረች:: በማግሥቱ ሰውዬው በገባላት ቃል መሠረት ወደ ሻጩ ሠፈር ወሰዳት:: ለሻጩም የሜሪን ጥረት ነገረው:: ሻጩ ታሪኳን ከሰማ በኋላ:- "በጣም አዝናለሁ፤ የምሸጥላት መጽሐፍ ቅዱስ የለኝም" ሲል ሜሪ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች::

ልቅሶዋን ሲያይ የሻጩ ልብ ራራ፤ እንዲህ አላቸው:- "አከሌ የሚባል ሰው አስቀምጥልኝ ብሎኝ በአደራ ያስቀመጥኩት አንድ መጽሐፍ ቅዱስ አለ፤ የፈለገውን ይበለኝ! መጽሐፍ ቅዱሱን ለሜሪ አሸጥላታለሁ!" ብሎ አምጥቶ ሰጣት። ሜሪ መጽሐፍ ቅዱሱን እቅፍ አድርጋ የደስታ ልቅሶ ጀመረች::

እነዚህ ሁለት ሰዎች የሜሪን ጥረት ቢያደንቁም ይህ ችግር የሚወገድበት ዘዴ መኖር አለበት ብለው መመካከር ጀመሩ። በሎንዶን ከተማ ውስጥ አነስተኛ የክርስቲያን ጽሑፍ አታሚ ነጋዴዎች ሕብረት መኖሩን ያውቃሉ:: ይህን ጉዳይ ለእነርሱ ማሳሰብ አለብን ተባባሉ:: ሻጩ አንድ ቀን ወደ ሎንዶን ሄዶ ለነኚህ ክርስቲያን ወንድሞች የሜሪ ጆንስን ታሪክ ነገራቸው:: በሜሪ ታሪክ የእነርሱም ልብ ተነካ:: መጽሐፍ ቅዱስ እያሳተምን ለእንግሊዝ ሕዝብ የሚያቀርብ ድርጅት እናቋቁም ተባባሉ:: ከመሃከላቸወ አንዱ ብድግ ብሎ ለምን ለእንግሊዝ ብቻ ለመላው ዓለምም ጭምር አንጂ ብሎ ሃሳብ በማቅረቡ የእንግሊዝና ውጭ አገሮች መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ሊቋቋም ቻለ:: አላማውም ሰዎች ሊገዙ በሚችሉት ዋጋና በቀላሉ ሊያገኙ በሚችሉበት ሁኔታ ማቅረብ ነበር:: ይህ የሆነው በ1804 (በ1797 ዓ.ም) ነበር::

ከአስራ አምስት አመት በኋላ የአሜሪካም መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ተቋቋመ። በሌሎች አገሮችም መቋቋሙን ቀጠለ:: ማሕበሩ በኢትዮጵያ ሥራውን የጀመረው በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ሲሆን ሙሉውን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ





ለመጀመሪያ ጊዜ በ1879 ዓ.ም ነበር ያሳተመው:: የመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱሲ ይኼው አትም ነበር። የዮሐንስ 3፥1-2 በዚያ ትርጉም እንዲህ ይነበባል:-

"ከፈሪሳውያን አንድ ሰው ነበረ ስሙ ኒቆዲሞስ የአይሁድ አለቃ:: ይህ ወደ የሱስ መጣ በሌሊት አለውም። እኛ እናውቃለን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ መምህር ሆነህ። አንድም የሚችል የለም ተአምራት ያደርግ ዘንድ አንተ የምታደርጋትን እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ካልሆነ በቀር"::

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንድ የሊቃውንት ቡድን (ኮሚቴ) አቋቁመው ቤተ መንግሥት ቢሮ አደራጅተውለት፣ ይህ የ1879 ዓ.ም ትርጉም ተሻሽሎ በዘመናዊ አማርኛ እንዲዘጋጅ አደረጉ:: የተሻሻለው ትርጉም በ1954 ታተመ:: በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ቅዱሰ ይህንን ትርጉም ነው:: ይህ ትርጉም በእንግሊዝኛ KJV (King James Vesion) እንደሚባለው በአማርኛ "ቀኃሥ" እየተባለ እንዲጠቀስ አፈልግ ነበር:: አሁን አሁን በስተርጅናዬ ዘመን ደምበኛ ደራሲያን መጻሐፍት ውስጥ "ቀኃሥ" ትርጉም ተዘውትሮ ሳይ ደስ ብሎኛል::

## ሁሉንም ቤተ እምነቶች በማሕበሩ ሥራ ማሳተፍ

ሥራዬን ስጀምር የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን በማህበሩ ሥራ ለማሳተፍ ፈለግሁ። ስለዚህም በማውቃቸው አባ ገብረ ሚካኤል የተባሉ የካቶሊክ ቄስ አማካይነት በዚያን ጊዜ ሃላፊ የነበሩትን (ያኔ ካርዲናል አልነበራቸውም) ለመተዋወቅ ሄድሁ። "በቫቲካን ሁለት" መመሪያ መሰረት በመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ሥራ እንዲሳተፉ ከሮም መመሪያ ተሰጥቶአቸው ነበር፤ በነገሩ ሲያስቡበት እንደነበር ነግረውኝ ለመተባበር ዝግጁ መሆናቸውን ገለጹልኝ፤ በመሆኑም በመማከርቱ ላይ ሦስት ሰው እንዲወከሉ ጠየቅኋቸው። እንዳሉት አደረጉ። አባ ገብረ ሚካኤልንና ፥አቶ ዮሴፍ አስቤ እና እና ኪዳነማሪያምን ሰየሙልኝ። አባ ገብረ ሚካኤል የግእዝ እና የእብራይስጥ ቋንቋ ያውቁ ስለነበር መጽሐፍ ቅዱስን በቀላል ቋንቋ ከተረጎሙት አንዱ ሆኑ::

ከሁለት አመታት በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ሥራ የኦርቶዶክስ ቤተ ክኀነትን ሙሉ ትብብር ፈለግሁ:: ዶክተር ጌታቸው ኃይሌን ወደ አባታችን ወደ ፓትርያርኩ አቡነ ቴዎፍሎስ ሙቼ ትወስደኛለህ? ስል ጠየቅኹት:: ቀጠሮ አስይዞ ወሰደኝ። በቀጠሮአችን ቢሮአቸው ስንደርስ ደጃፍ ላይ እርሳቸውን ለማነጋገር የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች ተኮልኩሰው አየን:: እኛም ተሰሰፍን ጥቂት ከቆየን በኋላ ዶክተር ጌታቸው ልዩ ጸሐፊያቸውን "የመጣነው ቀጠሮ ተቀብለን እኮ ነው" ሲለው በውስጥ ስልክ እንዲያስታውሳቸው ነገረው::

ዶክተር ጌታቸውም ቴሌፎን ደውሎ "አባታችን፣ ጤና ይስጥልኝ፣ 'አቶ ሚሊዮን መስቀሎን ሊስም' መጥቶ እዚህ ነን፤" አላቸው። 'መስቀል ሊስም?' የሚሰው አነጋገሩ ከው አደረገኝ:: መስቀል ልስም? ምን ላደርግ ነው? ገብቼ ሰላምታ ለመስጠት እጄን ልዘረጋ ነው? እንዲህ አይደረግም:: ከራሴ ጋር ተሟገትኩ። ዓላማዬ መጽሐፍ ቅዱስ የኦርቶዶከሶችም መሆኑን በይበልጥ እንዲያስቡ ለማድረግ ነው እያልኩ ላስብ ግቡ ተብለን ገባን:: መስቀል ስመን ቁጭ አልን። "የመጣሁት አገልጋዮ እንደ መሆኔ ከብጹዕነትዎ ምክርና ምሪት ለለ ምጠብቅ ነው" አልኳቸው። በጭውዉታችን የዱሮውን መጽሐፍ ቅዱስ በዘመናዊ አማርኛ እንዲያዘጋጁ ግርማዊ ጃንሆይ በሰየሙት ኮሚቴ ላይ እንደ ነበሩ ስምቼ ስለነበር ውይይታችንን እንያ ጀመርን ይህንኑ ጠቅስኩላቸው:: በወቅቱ ስለ ነበራቸው አንድ ቅሬታ አነሱልኝ፤ እንዲህ ሲሉ:-

"የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ 'ሐሰት 'በማለት ፈንታ 'ውሸት' መባሉ ቅር እንዳላቸው ነገሩኝ:: ሌላው የግርማዊ ጃንሆይ መቅድም መካተት የነበረበት በስልሳ ስድስቱ እትም ላይሆን፣ ለማንያ አሃዱ (፹፩) ላይ እንዲሆንና፣ እስዚያም አዲስ ኪዳን ለብቻው ሲታተም ብቻ እንዲሆን ወስነን የነበረው። እንድምመለከተው አሁን ቁንጽሉን (66ቱን) መጽሐፍ ቅዱስ ስታትሙ መቅድሙን ማስገባታችሁ ትክክል አይደለም" አሉኝ።





ወደ ቢሮዬ መጥቼ ኀትመቶቹን ስመረምርና ሳጠያይቅ BFBS መጀመሪያ ስልሳ ስድስቱን ሲያሳትም ጃንሆይ የጻፉት መቅድም አልተካተተም ነበር:: ሚስተር ብሊር እንደነገሩኝ ስልሳ ስድስቱን ማባዛት እንደ ተጀመረ ለመግለጽ ያንን ትርጉም በቆዳ ጠርዘው ለጃንሆይ በአበረከቱ ጊዜ ጃንሆይ: "እኛ የጻፍነው መቅድም ለምን አብሮ አልታተመም?" ሲሏቸው "ወደፊት በሚታተመው ይገባል" በማለት አስባልስው እንደ መለሱላቸው ነገሩኝ::

ከጊዜ በኋላ ቄስ ዕዝራና ባለቤቱ ወይዘሮ ገነት ወደ ቤታችን መጥተው ነበር:: በወቅቱ ግደይ ናታንን ወልዳ ስለነበረ አራስ ጥሪ ይዘው ነበር የመጡት:: በዚያን አለት ቄስ ዕዝራ: "ብለህ ብለህ የቄስ መስቀል መሳም ጀመርህ?" አለኝ። እንዴት እንዳወቀ ጠየኩት:: እርሱም አቡነ ቴዎፍሎስን ቢሮአቸው ሄዶ ሲጎበኝ እኔ አዳደረግሁት መስቀላቸውን ስሳልሳመ ሲውቅሱት፣ "አቶ ሚሊዮን መስቀላችንን ስሟል፤ አንተ ግን . ." እንዳሉት ነገረኝ:: የኔ የእርሳቸውን መስቀል መሳም ትልቅ ጉዳይ ሆኖ ከረመ:: እኔ ይህን ያደረግሁት መጽሐፍ ቅዱስ የኦርቶዶክስም መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስረዳት በማደርገው ጥረት እንዲረዱኝ ነበር።

## የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ምስረታን ማጠናከር

መማከርት ጉባኤው በሰጠኝ መመሪያ መሠረት ሌላው ትኩረቴ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ምስረታ ላይ ነበር የሆነው:: ለዚህም እንዲረዳኝ የሜሪ ጆንስንን ታሪክ በአጭሩ ጽፌ፣ በመጨረሻው ላይ ሰዎች የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አባል እንዲሆኑ የሚጋበዝ ነበር:: ያቺ ወረቀት ለመጀመሪያ ጊዜ ታትማ ስትመጣ ቢሮዬ ሆኜ እያነበብኳት እያለ የባፕቲስት ሚስዮናዊ የሆኑት ሚስተር ሰከመን ወደ ቢሮዬ ገቡ:: ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ጽሑፏን አቀበልኳቸው። እርሳቸውም እዛው አንብበው ስማቸውን ሞልተው፣ የመመዝገቢያ ሁለት ብር ለጡኝ፤ ተቀብዬ የመጀመሪያው አባል አድርጌ መዘገብኳቸው። በዚሁ ቀጠልሁ።

በምሥረታው አንዱ ትልቁ ነገር ማሕበሩ የሚመራበት መተዳደሪያ ደንብ ማዘጋጀት ነበር። የአሜሪካንን፣ በአፍሪቃ የማደጋስካርና ጋናን በመመልከት በተለይ ከአሜሪካው ጋር የሚመሳሰል መተዳደሪያ ደንብ ነደፍሁና ለመማከርት ጉባኤው አቀረብሁ:: ጉባኤው ይህን በሚመለከትበት ቀን ንድፉን አንብበው አንዲመጡ ልኬአለሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ ጥቂት ከተወያዩ በኋላ ሦስት አባላት ኮሚቴ (እኔና ሁለት አባላት) ተሰየምን፤ ረቂቁን ጉባኤው ካየው በኋላ ለህግ አዋቂም አሳይ ተባልሁ:: መተዳደሪያ ደንቡን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሜ ለምክር አስተያየት ኢንዲሰጡበት በዚያን ጊዜ የUBS ዋና ጸሐፊ ስነበሩት ለዶክተር ቤጉዊን ላኩላቸው:: እኚህ ሰው ለጉብኝት መጥተው በነበረበት ጊዜ ከእርሳቸው ጋር በመነጋገር አስተያየታቸውን አካተትሁ:: የአማርኛውንና እንግሊዝኛውን ለነድ ለጉባኤው ስናቀርብ ከቡር አቶ አማኑኤል በተለይ እንግሊዝኛውን በትኩረት በመመልከት ብዙ ለውጥ አደረጉበት።

ይህን ደንብ ስማዘጋጀት ብዙ ጊዜ ፈጅቷል:: የሕንጻ መሥሪያ ቦታ እንዲሰጡን ጃንሆይ ፊት በቀረብን ጊዜ የማሕበሩ የበላይ ጠባቂ እንዲሆኑ ጠይቀናቸው ስለ ነበር ግርማዊ ጃንሆይም የማሕበሩ የበላይ ጠባቂ መሆናቸው ተገለጸ። ደንቡ ከተዘጋጀ በኋላ ከመንግሥት እውቅና እንዲያገኝ በደብዳቤ አመልክተን አምስት ሰዎች በመሥራችነት (አንዱ እኔ) አስመዘገብን::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሕንፃ ግንባታ

ለመጽሐፍ ቅዱስ ማበር የተውኩት ቅርስ የመስሪያ ቤቱ ቢሮና መጻሕፍት ማከማቻ ህንጻ ነበር። በኋላ ግን ደርግ ሕንፃውን ወረሰው:: እኔ ሥራውን ስጀምር የተረከብኩት በግርማዊ ጃንሆይ ዘመን ፒያሳ ላይ በ1926 (እኤኦ) BFBS ገንብቶት የነበረውን ሕንፃ ነበር። ያ ሕንፃ ለዋና ጸሐፊው መኖሪያና የመጽሐፍ ቅዱስ ቤት (BIBLE HOUSE) እንዲሆን ታስቦ ነበር የተሠራው።





ሕንፃው በብዙ ምክንያቶች ለእኔ ምቹ አልነበረም:: ከላይ እንደ ገለጽኩት ለመኖሪያነት ስላልተስማማኝ ሌላ ቦታ ሄጀ ተከራይቻለሁ፤ እኔ ልኖርበት የታሰበውን ፎቁን አከራየሁት። መጻሕፍት ለማከማቸም ጠበበኝ፤ ለቢሮነትም አልተስማምኝም። ብዙ ጊዜ በዚያ የሚያልፉ ጓደኞችቼም ሆኑ የማውቃቸው ሰዎች:- በዚህ ስናልፍ አስታወስንህ፤ ታዲይስ እንድምን አለህ በማለት ጎራ ይሉ ነበር:: ለሰላምታ የሚመጡትን ሁሉ ሻይ ቡና መጋበዝ ነበረብኝ::

ጊዜዬን የሚበላና የሚያስቸግር ጉዳይ ነበር። ነገሩ ሁሉ ሲደራረብብኝ ያንን የመንገድ ዳር ቢሮ አከራይቼ ለማያዊ ሕንፃ ፎቅ ላይ ባለ ሁለት መኝታ ቤት ተከራየሁ ለእኔ ቢሮ፣ ለጸሐፊዬና ለሂሳብ ሠራተኛው፣ በኋላም ለቀጠርሁት ጉዳይ አስፈጻሚ ቢሮ በመሆን አገለገለኝ። እዛ እየሰራን ነበር ለመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አራት ኪሎ አደባባዩ አጠገብ አዲስ ሕንፃ ያሠራሁት። በደርግ ከተወረሰ በኋላ እኔ ለቦርድ መሰብሰቢያ ያቀድኩትን ጓድ ለገሠ አስፋው ቢሮው አድርጎት እንደ ነበር ለምቼያለሁ:: ግንባታውም የተከናወነበት መንገድ አስደናቂ ነበር::

***

እንደዚህ ያለ ፕሮጀክት መቼም ብዙ ተግዳሮት አለው። መጽሐፍ ለማከማቻትና ስመሸጫ፣ ለቢሮም ቦታ ጠበበኝ በማለት ለUBS አቤት አልኩ። የሚስማማ ቤት ተከራይቼ መውጣት እንደምችል አስታወቁኝ። ሥራውን የመጠነ ተሰማሚ ቤት ላገኝ እንደማልችል፣ ይልቁንም የሚሻለው ሕንፃ መሥራት እንደ ሆነ አጥብቄ ወተወትኳቸው:: በቀላሉ አልተረዱኝም ነበር፤ እንዲያውም:- «እኛ ገንዘብ የምናሰባሰበው ለመጽሐፍ ቅዱስ ግዥ እንጂ ለጡብና ለሲሚንቶ አይደለም» አሉኝ። በዚህም ተስፋ አልቆረጥኩም:: ሕንፃውን ለማሰራት ስንት ገንዘብ እንደሚፈጅ፣ የሚገነባበት መሬት መጠን፣ እና የሠላሰሉትን ጥያቄዎቻቸውን ለማስረዳት ሞከርኩ:: ተለሳለሱልኝ::

መሬቱን ጃንሆይ ሰጡን፤ ለሕንጻው ፕላን ወጣ፤ ማሠሪያው ተገመተ:: ከጠቅላላ ወጪው ካገር ቤት 20% ያህል ለማሰባሰብ እንድንሞክር ታቀደ:: በአቶ ኃይሉ ወልደ ሰማያት አማካይነት ከመካነ ኢየሱስ የጡረታ ቦርድ ገንዘብ እንደምናገኝ

ተሰፋ ተሰጠን፡፡ በዚህ ላይ UBS እንዲጨምርበት ተጠየቀና የሚሰጠው ታወቀ። ገንዘብ ማሰባሰቡን ጀመርን።

ካገር ቤት ገንዘብ ለማግኘት ብዙ ዘዴዎች የተጠቀምኩ ቢሆንም አድናቆት ያተረፈልኝ ግን መዘምራን (የሙሉ ወንጌል፣ የአንጦጦ መካነየሱስ፣ የአዲስ አበባ መካነ የሱስ፣ የቅድስት ሥላሴ ፣ የመርጋ አውራን መዘምራንን) አሰልፌ በአገር ፍቅር ማህበር አዳራሽ እንዲዘምሩ ማድረጌ ነበር። እነኚህን ሁሉ መዘምራን ሲዘምሩ ለመስማት ሕዝበ ክርስቲያኑ ቲኬት እንዲገዛ አደረግሁ። ተቃውሞዎችም ነበሩ፤ "አስረሽ ምቺው በሚደረግበት ቦታ መንፈሳዊ መዘምራንን ለገንዘብ ብለህ እንዴት ትሰበስባለህ?" ያም ሆነ ይህ ተዘመረ፡፡ ብዙ ሰዎችም መጡ። ዝግጅቱ በቀ. ኃ. ሥ. ቲያትር ቤት (አሁን ብሔራዊ ቲያትር ቤት) ግርማዊ ጃንሆይም በሚገኙበት ይደገም ተባለ፡፡ ቲኬት መሸጡን ተያያዝነው፤ ብዙ ሰዎች አገዙን፡፡

ግርማዊነታቸውም አጃቢዎቻቸውን አስከትለው ተገኙልን፤ ግን ሳይከፍሉ ነበር የገቡት። ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም ስለ ማሕበሩ መግለጫ ከአጭር መንፈሳዊ መልእክት ጋር ሰጡ፡፡ መዘምራን በዚያ ዘመን ዝነኛ የነበሩትን መዝሙራት «ያየኛል ወይ፣ ሰላም አለኝ ... የመሳሰሉትን መዝሙሮች በቡድንና በግል (ሶሎ) በተራ በተራ ዘመሩ፡፡ የመዝሙሮቹ ግጥምና ጠቅላላው የዕለቱ ከንውን በጋዜጣ በሰፊው ተዘገበ፡፡ በዚያን ዘመን እነኚህ መዝሙሮች በሕዝብ ዘንድ አይታወቁም ነበር።

በማግሥቱ ክቡር አቶ አማኑኤል ሰልከ ደውለውልኝ "ጃንሆይ አሥር ሺህ ብር ሰጥተውሃል፤ "ነገ ወደ ጽሕፈት ምንስቴር ሄደህ ጠይቅ" አሉኝ። በተነገረኝ መሠረት ወደ ጸሐፊ ትዕዛዝ ተፈራ ወርቅ ቢሮ ሄድኩ፡፡ አስር ሺህ ብር እንዲሰጠኝ ለዋናው ግምጃ ቤት የተጻፈልኝን ደብዳቤ ተቀብዬ ወደ እዚያው አመራሁ። ሞዴል ስድስት ላይ አስር ሺህ ብር ጽፈው አስፈርመው ሊሰጡኝ ገንዘብ ያዡ ገንዘቡን ሊቆጥር ሲጀምር "በቼክ ልወስድ አችላለሁን?" በማለት ጠየቅኩት፡፡ በቼክ ይሰጠው የሚል ደብዳቤ ከጽ/ሚኒስቴር ማምጣት እንዳለብኝ ሲነግረኝ በጥሬ ብር መረከቡ ተሸለኝ፡፡






አንድ መቶ ባለ መቶ ብር ቆጥሬ አስር ሺህ ብር ኮቴ ውስጥ አድርጌ ወጣሁ። ወደ ሾልስ ዋገን መኪናዬ ስሄድ ግራ ቀኝ እየተገላመጥኩ ነበር፡፡ መኪናዬን አስነስቼ ወደ ቢሮዬ ሸመጠጥሁ፡፡ ቢሮዬ የደረስሁት ለሰባት ሰአት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ ነበር፡፡ እንደ ደረስኩ ወደ ጸሃፊዬ ወደ እሳመኑች ኩምሳ ቢሮ ገብቼ በሩን ከኋላዬ ዘግቸቼ፡ "ይሄውልሽ፣ ይህ ጃንሆይ የሰጡን አስር ሽህ ብር ነው፤ አሁን ባንክ ሊዘጋ ስለሆነ ከሰአት በኋላ ሽፈራውን አስከትለሽ ሄደሽ ባንክ አስገቢ። እስከዚያ አሁን አንድ ቦታ ደብቂው" አልኳት፤ እንደ ተባባልነው ከሰአት በኋላ ባንክ እንደ ተከፈተ አስገባችና ተመለሰች፡፡ ባንክ ያስገባችበትን ሰነድ ስታሳየኝ "እፎይ እግዚአብሔር ይመስገን" አልሁ፡፡ ያኔ አስር ሺህ ብር ዋጋው እጅግ ብዙ ነበር።

ሕንፃ ተሠርቶ አለቀ፡፡ ጃንሆይ መጥተው መርቀው ከፈቱልን፡፡ ለምረቃው ግቢያችን ሲገቡ አበባ በመስጠት የተቀበላቻቸው ሩት ሚሊዮን ነበረች፡፡ ጃንሆይ የወርቅ ሳንቲም ሰጧት፡፡



ጃንሆይ አዲሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ህንፃ ሲመርቁ ግቢ ሲገቡ ሩት አበባ ስታበረክት



አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ህንፃ ምረቃ

## ቃሉን የማሰራጨት ሥራ

ዋናው ኃላፊነቴ የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች ሊገዙ በሚችሉት ዋጋ ለሰዎች ማቅረብ ነው ብያለሁ፡፡ ቃሉን በልዩ ልዩ መልክ፡- መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ አዲስ ኪዳን፣ ወንጌሎችና ምርጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በልዩ ልዩ መል አያሳተምን እናቀርብ ነበር፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ታሪክ ለምሳሌ የልደ ታሪክ ወይም የትንሳኤ ታሪክ አንወስድና አሳትመን እንዷን በሁለት ሳንቲ አንሸጣለን፡፡

አንድ ሺህ ወይም ከዛ በላይ ገዝቶ ቤተ ክርስቲያኒቱ ባለችበት አካባቢ ላሉ ሰዎ ለሚያድል 50% ቅናሽ አንሰጣለን። በአንድ ወቅት ኤልያስ ከባዓል ነቢያት ጋ ያደረገውን የውድድር ታሪክ አሳትሜ በዛው ላይ ጣኦት ማምለክ እግዚአብሔ የማይወደው ነገር መሆኑን ከአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ጨምሬ "ኢታምልክ ባዕደ.. የምትል ጽሁፍ 100,000 አሳተምኩ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ወጣቶችን አነታምራ ወልባን፡ የመስቀል በዓል አለት ደብረዘይት ሄደው ለህዝብ እንዲያድ አድርጌአለሁ። ያን ትራክት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በጣም ስለ ወደደቸው 50,000 አሳትሜላቸዋለሁ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መሸጫ ዋጋ 2.50 ነበር፡፡ አዲስ ኪዳን 50 ሳንቲም፣ ወንጌሎች ከአምስት ሳንቲም ጀምሮ ይሸጡ ነበር፡፡

በአምስት ሳንቲም ወንጌል መሸጥ ለምን እንዳስፈለገ የሚያብራራ ገጠመኝ ነበረኝ። አንድ ጊዜ ለአገልግሎት ዱራሜ ተጋብዤ ሄድሁ፡፡ እንደዚህ ላለ ነገር ከቢሮዬ ለወጣ የምሸጣቸው ልዩ ልዩ መጻሕፍት ይዤ አወጣለሁ፡፡ ስብከት በማይካሄድበት ጊዜ ለሰዎች መጽሐፍት አሸጣለሁ። ሁሉም እንደ ፍላጎቱና እንዳቅሙ ይገዛል፡፡ እንድ ልጅ አንድ የዮሐንስ ወንጌል እንድሰጠው ሲጠይቀኝ አምስት ሳንቲም አምጣ አልኩት፡፡ አስር ስንቲም ሰጠኝ መልስ ልሰጠው ስሞክር አጣሁ፡፡ "ሌላ ወንጌል ልጨምርልህ" ስለው፤ "አይ አምስቷን ሳንቲም አፈልጋታለሁ፤ የመጣሁት ከሩቅ ነው ቆሎ አገዛባታለሁ" አለኝ። ያለውን አስር ሳንቲም ግማሹን ለመንፈሳዊ ሕይወቱ አምስቷን ለሥጋው አደረጋት ማለት ነው።





የወንጌሏ ዋጋ ከአምስት በላይ ቢሆን ኖሮና ቢገዛት ጦሙን ይዉል ስለ ነበር ወንጌሏን አይገዛም።

ዋናው ጥረቴ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ስይቸገሩ እንዲያገኙ ማስቻል ነበር፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ወደ ሱቃችን መጥተው፣ ከኛ መጽሐፍ ቅዱስን በሁለት ብር ሂሳብ ገዝተው ለምእመናቸው በ2.50 እንዲያቀርቡ አደፋፍራለሁ። ኢትዮጵያን በመኪና እየዞረ የሚሸጥ ቡድንም ነበረኝ፡፡ በየኮንፍረንሱ፣ በየገጠሩ በየቤተክርስቲያን ሁሉ ይዞሩ ነበር፡፡ እኔም ከታደሰ እብዲሳ ጋር አንዴ ቁልቢ ገብርኤል ሂጄ ድንኳን ተከለን ሸጠናል፡፡ አግረ መንገዳችንንም ደደር ጎራ ብለን ስለነበር ከተማንና አከሊልን ይዘን እንዲረዱን አድርገናል፡፡ ሁለቱም ለመጀመሪያ ጊዜ ስለነበር በመኪና የተሳፈሩት እስከ ዛሬ ያስታውሱታል፡፡

## ቀለል ባለ አማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

እኔ የኢትይጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጠቅላይ ጸሐፊ የሆንኩ ሰሞን የአሜሪካን መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አዲስ የእንግሊዝኛ አዲስ ኪዳን አስተርጉማ Good News for Modern Man ብላ አሳትማ ነበር። ይህ አዲስ ኪዳን በአሜሪካን አገር በየሱፐር ማርኬት ውስጥ እንደሚሸጥና በጣም መወደዱን ሰማሁ። አንድ ኮፒ ለናሙና ተልኮልኝ አነበብኩት፡፡ በጣም ወደድኩት። በብዛት እንዲላከልኝ ጠይቄ ተላከልኝ፡፡ ሌሎችም የእኔ መማከርት ጉባኤ አባሎች በተለይ አባ ገብረ ሚካኤል ወደዱት፡፡ እርሳቸውና እኔ የእኛን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንድናዘጋጅ ተወያየንና ለቦርዱ አቀረብን፡፡ ቦርዱም ተስማማና ሃሳባችንን ለUBS እንድገልጽ ተነገረኝ፡፡ መልስ ሲሰጡኝ "ያለን ትርጉም ለማሻሻል መሞከር ከባድ ከመሆኑም በላይ ብዙ ሰዎች የለመዱት ትርጉም ስለሆነ እንዲለወጥ አይፈልጉም፡፡ የሚሻለው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ያልሆነ ሰዎችም በቀላሉ የሚረዱት አዲስ ትርጉም መስራት ነው" አሉኝ፡፡ ስለ አተረጓጎም ዘመናዊ ዘዴ ለመማከርት ቦርድ አባላት ስልጠና ተሰጠ።

የዩ.ቢ.ኤስን ሃሳብ ተቀብለን ሶስቱም የእምነት ወገኖች (ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ወንጌላውያን) የሚቀበሉት ትርጉም ልናዘጋጅ አቀድን። ጉዳዩን ለአብያተ ክርስቲያናት በዝርዝር ስጽፍ ተርጓሚም እንዲጠቁሙ ጠየቅሁ። እንዲህ ያለውን ሃሰብ ለማስተናገድ ሳይችግራቸው አልቀረም፤ ሆኖም፡- ሊቀ ስልጣናት ሐብተ ማርያም ቄስ መከብብ አጥላውን ወከሉልን፡፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባ ገብረ ሚካኤልን ሰጠች፤ በዚያን ጊዜ የወንጌላውያን ሕብረት ድርጅት ስላልነበረ ከወንጌላውያን ምንም አልሰማሁም። በግሌ በመጠያየቅና በመመካከር አቶ መሰፍን ተስፋዬን ጠቆምሁ። ከስምምነት በስተቀር ተቃውሞ ስላልደረሰኝ ሦስቱን የትርጉም ሥራ አስጀመርን፡፡

ሦስቱ የሚተረጉሙትን በትንንሹ እያሳተምን አብያተ ክርስቲያናት ሃሳብ እንዲሰጡ አደረግን፡፡ ሥራው ሊጀመር ሲል ወደ ናይሮቢ ተዛወርኩ፡፡ በእቅዱ መሠረት ቡድኑ በሰኔ 1967 ዓ.ም መተርጎም ጀምረው አዲስ ኪዳን በሶስት አመት አልቆ ታተም። ብሉይ በ1975 ዓ.ም አለቅና ለህትመት ማዘጋጀቱም አልቆ "ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ" ተብሎ በ1980 ዓ.ም. መላው መጽሐፍ ቅዱስ ታተመ።

## የአለም መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች ጠቅላላ ስብሰባ በአፍሪቃ አዳራሽ

የመላው ዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበሮች ስብሰባን (1972 UBS WORLD ASSEMBLY) በመስከረም 1965 ዓ. ም በአፍሪቃ አዳራሽ አስተናገድኩ፡፡ ይህ ስብሰባ እኔን በውጪው አለም እንድታወቅ አደረገኝ፡፡ ስብሰባውን የከፈቱት ግርማዊ ጃንሆይ ነበሩ፡፡ አቡነ ቴዎፍሎስ ደግሞ በቡራኬ ዘግተዋል፡፡ የአቡኑ በዚህ ስብሰባ ላይ መገኘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በማህበራችን አመራር ዉስጥ እንዳለች ተጨማሪ ማረጋገጫ ነበር።

ስብሰባው ለአንድ ሳምንት ነበር የቆየው፡፡ በስብሰባው መሃል ሁላችንም ለሻይ ቤተ መንግስት ሄደን የግርማዊ ጃንሆይን እጅ ለመጨበጥም ችለናል። ስብሰባው የተካሄደው ወደ አዲሱ ህንጻችን እንደ ገባን ስሞን ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መጽሐፍ





ቅዱስ ማህበር የUBS ሙሉ አባልነት ያገኘቺው ያኔ ነበር። የመማከርት ቦርዱ የጣለብኝ አንዱ ሃላፊነት ተከናወነ ማለት ነው። የአፍሪቃን ማሕበሮች በአስተዳደር አማካሪነት (MANAGEMENT CONSULTANT) እንዳገለግል መጀመሪያ የተጠየቅሁት ያኔ ነበር፡፡ ማቅማማቴን የተመለከቱ አንዳንድ የUBS ባለስልጣኖች በሰራው ህንጻ ትንሽ ይኑርበት፤ ለአሁኑ እንተወው በማስት ተዉኝ። ግን በአመቱ ጥሪያቸውን አደሱና ወደ ናይሮቢ ለመሄድ በቃሁ።

## የቦርድ አባላት ምርጫ ስርዓት

ያን ጊዜ የጀመርኩት የማህበሩን ቦርድ አባላት በመላው አባላት የማስመረጥ ሥርዓት አሁንም በኢትዮጵያ መጽሃፍ ቅዱስ ማህበር እየተሰራበት ይገኛል። አባላት የሚገኙት በመላው ኢትዮጵያ ነው፡፡ እንኳን ከመላው ኢትዮጵያ በአዲስ አበባም ያሉትን አባላት በአንድ ቦታ ሰብስቦ የቦርድ አባላትን ማስመረጥ እንደማያዋጣ ተገነዘብሁ፡፡ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር እንደሚያደርገው አባላት ምርጫቸውን በፖስታ እንዲያካሂዱ ስልት ፈጠርሁ። ከሃያ አራቱ የቦርድ አባላት በያመቱ አንድ ሶስተኛው አግልግሎታቸውን ይጨርሳሉ፡፡ የአስመራጭ ኮሚቴ ይሰየምና ይህ ኮሚቴ ከአባላት መስፈርት የሚያሟሉትን ቢያንስ አስራ ስድስት ሰዎች ይጠቁማሉ፡፡ ስለእያንዳንዱ እጩዎቹ አጭር መግለጫ ይጻፋል። አባላት ከተጠቆሙት ስምንት ሰዎች ይመርጣሉ፡፡ ማን እንደተመረጠ በሚቀጥለው የአባላት አመታዊ ስብሰባ ላይ ይገለጻል፡፡ ምናልባት እኩል ድምጽ ያገኙ ቢኖሩ እዛው ይፈታል። በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር በደስታ ያገለግኩት ወቅት ነበር፡፡ በአስመራ በከፈትኩት ቅርንጫፍም ሆነ በአዲስ አበባ የነበሩኝ የሥራ ጓደኞቼ ጋር እንዋደድ ነበር፡፡

## ኃይሉ ወልደ ሰማያት

በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ሥራዬ በጣም የረዳኝ ሰው አቶ ኃይሉ ወልደ ሰማያት ነበር። በአማካሪ ቦርዱ ላይ እንደ አቃቤ ንዋይ የሚያገለግል ሰው አስፈለገ፡፡ ኸርብ ካስለር ይህን ሃሳብ ለአማካሪው ቦርድ ሲያቀርብ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በኮሙኒኬሽን ዲሬክተርነት የሚያገለግለው አቶ ኃይሉ ተጠቆመ። እኔና ካስለር ከርሱ ጋር ለመተዋወቅና የአማካሪው ቦርድ አባልና በዚያው ላይ አቃቤ ንዋይ እንዲሆን ለማግባባትና ለመጠየቅ ጎጆ ምግብ ቤት ምሳ ጋበዝነው።

አቶ ኃይሉ ጌታን ለማገልገል የሚፈልግ ስለ ነበረ ጥሪያችንን ተቀበለ፡፡ ካስለር የአቃቤ ንዋይነት ሃላፊነት ለመወጣት የሚችል መሆኑን በግሉ ለማወቅ ፈልጎ "በአየር መንገዱ አንተ የምታስተዳድረው በጀት አለህ ወይ? ካለህስ ምን ያህል ነው?" ብሎ ሲጠይቀው ካንድ ሚሊዮን ብር በላይ መሆኑን ገለጸለት፤ ጥሩ ነው በማለት አደነቀለት። ካስለር በኋላ ሲነግረኝ "ምላሹን ስለማ በራሴ አፈርሁ" አለኝ፡፡ ከአቶ ኃይሉ ጋር የተቀናጀነው እንዲህ ባለ ሁኔታ ሲሆን አገልግሎታችን ለዘመናት ቀጠለ። ለUBS Executive Committee አባልነት ከኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ጠቁሜው ለብዙ አመታት በዚህ ወሳኝ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ ላይና በአፍሪቃውም ኮሚቴ (UBS AFRICA RIGIONAL COMMITTEE በአጭሩ AFREC) ላይ ለብዙ ዓመታት አገልግሎአል። ለእኔ የአፍሪቃ ዋና ጸሐፊ (UBS AFRICA REGIONAL SECRETARY) መሆን ትልቅ ሚና ተጫውቶአል፡፡ የእርሱ ብርቱ ጥረት ባይጨመርበት ኖሮ ያ ታላቅ ኃላፊነት ባልተሰጠኝ ነበር።

ጥቂት ነጥቦች ስለ አቶ ኃይሉ ልጨምርላችሁ፡፡ እኔ ወደ ናይሮቢ ስዛወር ተከቶኝ ማሕበሩን እንዲመራ የተሾመው አቶ ጌታሁን ተ. ማርያም ነበር፡፡ እሱ ሲቀጥል ስላልፈለገ አቶ ኃይሉ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የነበረውን ኃላፊነቱን ትቶና ደመወዙንም ቀንሶ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ዋና ጸሐፊ ሆነ፡፡





በተጨማሪም ለአጭር ጊዜም ቢሆን በናይሮቢ ቢሮአችን አማካሪ (Supply Consultant) ሆኖ አግዞኛል።

ሉተራኖች አቋቁመውት የነበረው የብሥራተ ወንጌል ሲዘጋ ከናይሮቢ መንፈሳዊ የራዲዮ መልእክቶች ይተላለፉ እንደ ነበረ ይታወሳል፡፡ የመልእክት አቀራረባቸው እኔንም አቶ ኃይሉንም አላስደስተንም ነበር፡፡ ሁለታችንም የሚመለከታቸውን ሁሉ ሰብስበን መከርናቸው። ያ ምክክር የስዊድን፣ ኖርዌይና የአኛም ሜኖናይት ሚሲዮን ከላሉንጋ በመተባበር የወንጌል ስርጭት አገልግሎት (Gosple Broadcasting Service) የሚባለው ተቋም ተጀመረ። አቶ ኃይሉ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ተቋሙ ወደ አዲስ አበባ እኪመጣ ድረስ አገለገለ፡፡ እኔም የናይሮቢ ኮሚቴው ሰብሳቢ ነበርኩ። በራዲዮ የሚተላለፉት መልእክቶች በደርግ ዘመን ብዙዎች የሚጽናኑባቸው እንደ ነበሩ ይታወሳል፡፡

የናይሮቢውን ወንጌላውያን ሕብረትም ከሌሎች ወንድሞች ጋር ተባብረን አቋቁመናል፥ አብረንም አገልግለናል። ደርግ ሲገረሠሥ ያ ድርጅት ብሥራተ ወንጌል የሚለውን ስም አድሶ በመካነ ኢሱስ ቤተከርስቲያን መሪነት እንዲሠራ ወደ ኢትዮጵያ ተዛወረ። አቶ ኃይሉና ቤተሰቡ ወደ አሜሪካ እኛም ወደ ኢትዮጵያ ተመለስን። ለጊዜው ተለያየን፤ መለያየታችንን አልወደድነውም ነበር። በመሆኑም አሁን ሁለታችንም በለገጣፎ (ሮፓክ መንደር) ኩታ-ገጠም ቦታ ላይ ቤት ሠርተን ጎረቤታሞች ነን። የሁለታችንን ግቢ የሚያገናኝ የግል በርም አበጅንለት፤ በመንደራችን ኗሪዎች ዘንድ ወንድማማቾች በመባል እስከንታወቅ ድረስ ወዳጅነታችን እስከ እርጅና እስከ ሽምግልና ዘለቀ፡፡

# ምዕራፍ 10

## በአፍሪቃ ደረጃ ማገልገል

### ወደ ናይሮቢ መዘዋወር

ወደ ናይሮቢ እንድዛወር መጀመሪያ የተጠየቅሁት በመስከረም 1965 ዓ.ም አዲሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ሕንፃ እስርቼ ባስመረቅኹበት ሰሞን መሆኑንና ጥያቄውንም ለመቀበል እንደ አቅማማሁም ከላይ ጠቅሻለሁ፡፡ በአዲሱ ሕንፃ የመሥራት ወረት ከማጣጣም ሌላ አንዱ ምክንያቴ ከአገሬ ውጭ ለመኖር ስላልፈለግኹ ነበር፡፡ በእኔ የወጣትነት ዘመን ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ውጭ መኖር እንደማይፈልጉ አንባቢ ልብ ይበል፡፡ አብዮት የሚባለው ክስተት ፈንድቶ ደርግ አገሪቱን እስከ ተቆጣጠረበት ጊዜ ድረስ ውጭ አገር ለትምህርት ተልከው፣ በዚያው ቀልጠው የቀሩ ተማሪዎች በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡

በዱሮ ዘመን በአሜሪካን አገር ስታቲስቲክ መሠረት ከውጭ አገር ለትምህርት አሜሪካ የሚሄዱ ተማሪዎች ወደ አገራቸው በመመለስ ኢትዮጵያውያን በአንደኛ ደረጃ ይቀመጣሉ ይባላል። የራሴንም አስታውሳለሁ፤ አሜሪካኖች "አሜሪካን ትወዳለህ?" ሲሉኝ አዎን እላቸዋለሁ። "እዚህ ለመኖር ትፈልጋለህ?" በማለት ሲጠይቁኝም እንደለድብ አቆጥርባቸው ነበር፡፡ "ትምህርቴን እንደጨርስሁ ላልውል ላላድር ወደ አገሬ እመለሳለሁ" ስላቸው፣ ምንተፍረታቸውን "እንዳገር ምናለ?" ይሉኝ ነበር፡፡

ጃንሆይ አንድን ሰው አምባሳደር ወይም ቆንስላ አድርገው ወደ ውጭ ሲልኩ ያንን ሰው ከፊታቸው ገለል ለማድረግ ፈልገው ነው ይባላል። ለምሳሌ በአንድ ወቅት ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ኃዋርያት ከአርሻ ሚኒስቴርነት ተነስተው የዘውድ አማካሪ ተብለው ነበር፡፡ ወዳጄ ዶክተር በየነ ጭምጭአይበሉ ጎረቤታቸው





ስለ ነበር፣ እኔ ከባህር ዳር መጥቼ እርሱ ዘንድ አርፌ ነበርና፡ "እንሂድና ሹመት ያዳብር እንበላቸው" አለኝ፡፡ ወደ ቤታቸው ሄድን፤ እርሳቸው አልነበሩም፤ ባለቤታቸውን "እንኳን ደስ አላችሁ፤ ሹመት ያዳብር" ለማለት ነው የመጣነው" ስንላቸው፡ "ካውንስላ አድርገው ወደ አንድ አገር ስላልላኩን ደስ ብሎናል" አሉን።

ወደ ተነሳሁበት ርዕስ ጉዳይ ልመለስ፤ በጥቅምት ወር 1966 ዓ.ም ወደ ናይሮቢ የመዛወሩ ጥሪ እንደገና መጣ። አገሬን፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቴን፣ የጀመርኩትን የኢትዮጵያን መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ቀጣይ ሥራ ትቼ ወደ ናይሮቢ መሄዱ በጣም ከበደኝ፡፡ ስለ ጥሪው ለግደይ ስነግራት ሳታቅማማ ለአምስት አመት ያህል ወጣ ብለን እንምጣ አለች። በዚያን ዘመን በቤተ ክርስቲያን የነበረኝ ትልቁ ሥራዬ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቀ መንበርነት ነበር፡፡

የቀረበልኝን ጥሪ ለሌሎች በማካፈል ምክር መጠየቅ ቀጠልኹ፤ በዚያን ጊዜ የኢ.ት.መ.ቅ.ማ. ፕሬዚደንት ለነበሩት ለክቡር አቶ አበበ ረታ ወደ ናይሮቢ እንድዛወር መጠየቄን ነገርኳቸው፡፡ "ወደዚያ መሄድህ ማሕበራችንን ይጠቅማል፤ ለኢትዮጵያም ክብር ነው፤ ጥሪውን ብትቀበል መልካም ነው" አሉኝ፡፡ ከአቶ ኃይሉ ወልደሰማያት ጋርም ተወያየሁ፡፡ ሌላው ሸክም የሆነኝ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ስለነበር ጥሪውን ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ገልጬ ስንወያይ ወንድም ጥላሁን በየነ "ማናችንም ብንሆን የማንተካ አድርገን ራሳችንን ማሰብ የለብንም፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አረጋግጥ እንጂ ያም አገልግሎት ነው" አለ፡፡ ለመሄድ ወሰንኹ፡፡

የደረሰኝን ጥሪ ለኢ.ት.መ.ቅ.ማ. ቦርድ ገለጽኹ፤ ተወያዩበት፤ ሊለቁኝ ወስኑና ተተኪ ሰው ይፈለግ አሉ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር የሚተካኝ ማሰብ ጀመርኹ። በዚያን ጊዜ እንትሮፐ (Antrop) በሚባል መድኃኒት አስመጪ ኩባንያ ዉስጥ ታላቅ ሃላፊነት የነበረው አቶ ጌታሁን ተክለማርያም የሚባል ወንድም ነበር፡፡ እሺ ቢል ጥሩ ተተኪዬ እንደሚሆን አቶ ኃይሉና እኔ መከርን። የኢ.ት.መ.ቅ.ማ. ቦርድ "የምታስበው ሰው አለህ ወይ?" ሲሉኝ ሳላመናታ አቶ ጌታቸውን ጠቆምኹ።

አብዛኞቹ የቦርድ አባሎች የሚያውቁት ሰው ስለነበረ ያለ ብዙ ክርክር አቶ ጌታሁን ጥሪ እንዲደርሰው ተስማሙ:: እንደተጠየቅም እሽታወን ገልጾ ሥራውን ተረከበኝ::

የማሕበሩ አርማ ያለበት ቀለበት፣ የሸሚዝ መያዣዎች ተሸልሜ ግደይም የአንገት ሃብል ተሸልማ ተሸኘን። የማህበሩም ሠራተኞች በአዲስ አበባ ምግብ ቤት አዳራሽ አራት ጋብዘውን ከላይ በጃርት ጠጉር ያጌጠ አግሩ የአጋዘን ቀንድ የሆነ ክብ ጠረጴዛ አበርክተውልን ሸኙን:: ያ ጠረጴዛ አሁንም ጌጣ ጌጥ አያሰቀመጥን እንጠቀምበታለን::



ናይሮቢ እንደገባን መኖሪያ ቤታችን ግቢ፤ 1966 ዓ.ም.

ወደ ናይሮቢ ሕይወታችን ትረካ ከመግባቴ በፊት አንድ ነገር ላንሳ:: በኢትዮጵያ ከሠራሁት በደስታ የማስታውሰው በአሥመራ ቅርንጫፍ መከፈቴን ነው:: በቅርንጫፉ መከፈት በአሥመራ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ተደስተው ነበር:: በየአመቱ ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን በአል በከተማው የማዘጋጃ ቤት አዳራሽ አዘጋጅ ነበር:: በመጀመሪያው ስብሰባ የግ.ቀ.ኃ.ሥ. እንደራሴ ልዑል አሥራተ ካሣ ተገኝተው ነበር።





ወደ ናይሮቢ ከመሄዴ በፊት የአሥመራውን ኮሚቴ ልሰናበት ሄጄ ነበር። ወቅቱ የአብዮት ፍንዳታ ጊዜ ነበር:: በዚያን ጊዜ ከየመሥሪያ ቤት ሰዎች ብሶታቸውን ለማግለጽ ወደ አደባባይ ይወጡ ነበር:: ብሶቱንም የኢትዮጵያ ራዲዮ ያስተጋባል፤ አሥመራ ሳለሁ ብሶታቸውን የገለጹ የቤተ ክህነት ሠራተኞች እንደ ነበሩ ሰማኹ። "እኛስ ወንጌላውያን ብሶት የለንም እንዴ" ስል ራሴን ጠየቅኹ። ይህንንም ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ለሠፈር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጸሎት ጓዶቼ አካፈልሁ:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አባላቱ ጥላሁን ኃይሌ፣ ካፒቴን ዮሐንስ፣ አብርሃም ተሰፋ ሚካኤል ነበሩ።

ከእነርሱ ጋር በነገሩ ተመካከርንና የተወሰኑ መሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ትንሿ የቦርድ መሰብሰቢያ ክፍል እንዲገኙ አደረግን። ያቺ ስብሰባ ጭቆናችንን ለማሰማት ሳይሆን የራሳችንን ጉድለት የቃኘንበት ጊዜ ሆነች:: በተለይም የነቢይነት ኃላፊነታችንን በድፍረት አለመስራታችንን ተገንዝበን፤ መጸለይና መናዘዝ እንዳለብን ተስማማን:: የኑዛዜን መልእክቶች ወንድም መሰፍን ተስፋዬ አዘጋጅቶ በብሥራተ ወንጌል እንዲተላለፍ ወሰንን:: ዘወትር ቅዳሜ ጠዋት በዚያው ቦታ እየተሰበሰብን መጸለይ ጀመርን:: የዚያች ቅዳሜ ጠዋት የመሪዎች ጸሎት ስብሰባ እድገ በላንጋኖና በናዝሬት ለመሪዎች ልዩ ኮንፈረንስ ማዘጋጀት ደረጃ ደረሰች:: በኋላም የአሁኑ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ኅብረት ለመመስረት ምክንያት ሆነች።

ወደ ናይሮቢ ለመሄድ የተንቀሳቀስነው አብዮቱ በጀመረበት ወቅት ነበረ:: ሰዎች "ከዚህ ውዝግብ ዉስጥ ልትወጡ ነው፤ እግዚአብሔር ይወዳችኋል" ይሉን ነበር:: ወደ ናይሮቢ ለመሄድ የወሰንነው አብዮቱ ከመጀመሩ በፊት ስለነበር "እግዚአብሔር ሁላችንንም ይወዳል" እያልሁ መልስ እሰጥ ነበር።

## ጃንሆይ ከዙፋን የወረዱ ጠዋት

በናይሮቢ ትምህርት የሚጀምረው በነሐሴ ወር መጨረሻ ስለነበር፣ ነሐሴ 15 ቀን 1966 ዓ.ም ቤተሰቤን ይዤ ወደ ናይሮቢ ተጓዝን፡፡ ልጆቼን ትምህርት ቤት አስገብቼ ሥራዬንና ኃላፊነቴን በሥርአት ለማስረከብ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ። መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም አዲስ አበባ አሸብር ቤት ነበር የዋልኩት። የእንቁጣጣሽ ቀን እቤት ሆነን አንድ ሰው ጃንሆይን እንተ እያለ የፈጸሙትንና ያደርጉትን ሲናገሩ ሰማሁ፤ ሰውዬው በግዞት ለብዙ ዓመታት የቆዩ ሰው ነበሩ።

እንዲሁም ሬዲዮ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ዛሬ በዚች የዓመት መለወጫ በዓል ቀን የምናቀርብልህ መልካም ወሬ የለንም፡፡ ንጉሡ ለዘመናት በባዶ ሆድህ ከአዳላ ያወጣኸውን የወርቅ ሽያጭ ካስቀመጡበት የስዊዘርላንድ ባንክ እንዲያስመጡ ጠይቀናቸው እምቢ ብለዋል፡፡ ሌማትህ ባዶ ነው" በማለት መግለጫ ሲሰጥ ሰማኹ። ደጋግመው "ዛሬ ማታ በቴሌቪዥን የምናስተላልፈው ልዩ ፕሮግራም ስላለ የአዲስ አበባ ሕዝብና ንጉሡም እንዲመለከቱት እናሳስባለን" በማለት አስተዋወቁ። እንደሚታወቀው ፕሮግራሙ በወሎና ትግራይ ጠቅላይ ግዛት ተከስቶ ሺዎችን ስለ ጨረሰው ድርቅ ነበር። ያንለት ማታ ፕሮግራሙን አይቼ ስጨርስ እጅግ በጣም አዘንኩ፡፡ እንደ ብዙዎቹ ሁሉ እኔም በጃንሆይ ላይ ፈረድኩ፡፡

በማግስቱ ጠዋት አሸብር ከእንቅልፌ ቀስቅሶ አዋጅ ስማ አለኝ። ተነስቼ ማዳመጥ ጀመርን " . . . አንደኛ - ከዛሬ ጀምሮ ንጉሡ ከስልጣን ወርደዋል፤ ሁለተኛ - አልጋወራሹ ሕክምናቸውን ጨርሰው እንደ ተመለሱ የንግሥ ስርአቱ ይፈጸማል፤ ሦስተኛ- እስከአዚያ ድረስ 'የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊት፣ የአየር ኃይል፣ የብሔራዊ ወታደር ደርግ መንግሥቱን ይመራል፣ አራተኛ . . . " እያለ ቀጠለ።

ጥቂት ቆይቶ ራዲዮኑ ስለኔ አስደንጋጭ ዜና ተናገረ፡፡ "ከዛሬ ጀምሮ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አይበርም፤ አየር ማረፊያው ለሌሎች አየር መንገዶችም ዝግ ይሆናል" አለ። ወይኔ ቤተሰቤ ብዬ ጮህኩ፤ ወደ ናይሮቢ ስልክ አስመዝግቤ ቁጭ





ብዬ መጠባበቅ ጀመርሁ። መልስ የለም፤ ወደ ቢሮ ሄድሁና እዛው መጠባበቅ ጀመርሁ፤ "ለምን አታገናኙኝም?" ስል መስመር ስለተበላሸ ነው ይሉኛል፡፡ በኋላ ሳስበው ምንም አይነት ግንኙነት ከሌላው አለም ጋር ስለ ተቋረጠ ነበር።

መትረይስ የደገኑ የጂፕ መኪናዎች በከተማው ወዲያና ወዲህ ይራወጣሉ። በአንዳንድ ቦታዎች በአበባ የደመቁ ታንኮች ተጠምደው ቆመዋል፡፡ ታላቁ ቤተ መንግሥት በራፍ ላይ በጣም ትልቅ ታንክ ቆሞ አየሁ፡፡ አንደ አድል ሆኖ ሥራውን ያስረከብሁት አቶ ጌታሁንና እኔ በዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ፊት ለፊት አልፈን ወደ ካዘንቺስ ስንሄድ ኢዩቤልዩ ቤተመንግስት በር ፊትለፊት ልጆችና ጥቂት አዋቂዎችም ቆመው አየን፡፡ አስኪ እንመልከት ብለን መኪናችንን አቁምን ወረድ እንዳልን አንዲት ቮልስዋገን ከግቢ ስትወጣ አየን፡፡ ግርማዊነታቸውን የያዘቺው መኪና ነበረች፡፡ የት እንደሚወስዷቸው ለማየት ልንከተል ብንሞክር ተከለከልን፡፡ ምኒስትሮቻቸው ወደ ታሰሩበት ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር እንደወሰዷቸው ተረዳን። እኔና አሸብር ማታ በቴሌቪዥን አየተመለከትን ትላንት ማታ ያየነውን እያስታወስን ዋጋቸውን አገኙ ብለን ፈረድን። የወታደር አገዛዝ በአገራችን አየተጀመረ መሆኑንም ተረዳን። በጉዳዩ ከአቶ ጌታሁን ጋር ስወያይ "ለእነኚህ ወታደሮች ቢያንስ አስር አመት እሰጣቸዋለሁ" አለ፤ አስራ ስባት እመት ገዙ፡፡

ከናይሮቢ አፍሪቃን ለማገልገል የኢትዮጵያ የስራ ርከከቤን ጨርሼ ወደ ናይሮቢ ስመለስ የኢትዮጵያውን አብዮት የናይሮቢ ጋዜጦች 'አዝጋሚው መፈንቅለ መንግሥት' እያሉ ሲጠሩት አየሁ፡፡ "ያለ ምንም ደም" በመባሉም 'አድናቆት ለኢትዮጵያ ወታደሮች' ይገባል ተባለ፡፡ ይህ አባባል መደነቁ ያቆመው ስልሳዎቹ የጃንሆይ ባለ ሥልጣናት ከተረሸኑ በኋላ ነበር፡፡ የስልሳዎቹን መረሸን የሰማሁት የዩጋንዳ መ.ቅ.ማ. የዩ.ቢ.ኤሲ. ተባባሪ አባል በመሆንዋ በዛ በአል ላይ ለመገኘት ካምፓላ በተገኘሁበት ወቅት ነበር፡፡ ኢዲ አሚንም በዛ በአል ላይ ተገኝቶ ነበር፡፡ በስብሰባው ላይ ከውጭ የመጣነውን አስተዋውቀውን ስለ ነበር በሻይ ጊዜ ኢዲ

አሜን ሲጨብጠኝ "እኔ እንከባከባቸዋለሁ፤ ኃይለ ሥላሴን ወደ እኔ ላኳቸው" አለኝ።

ወደ ናይሮቢ የመጣሁት የአስተዳደር አማካሪ (Management Consultant) ለመሆን ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የአፍሪቃ ማሕበሮች ዋና ጸሐፊ (UBS Africa Regional Secretary) ኒውዚላንዳዊ ነበር፡፡ ቀደም ብሎ የሞሪሸየስ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ዋና ጸሐፊ ስለነበር በስልጠና ላይ ተገናኝተን ስለነበረ እንተዋውቃለን በጣም እንግባባም ነበር፡፡ እኔ ከኢትዮጵያ እንድመጣ ያደረገኝ እርሱ ነው፡፡ ስንብት ለመጠየቅ ማሰቡን ግን አላወቅሁም ነበር። ናይሮቢ መኖር በጀመርኩ በሰድስተኛው ወር ላይ ስንብት ስለጠየቀ እኔ በእርሱ ምትክ ዋና ጸሐፊ እንድሆን ተጠቆምሁ፡፡ ግማሹ የአፍሪቃ ሃገሮች ፈረንሳይ ተናጋሪ በመሆናቸው በተለይ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ባለማወቁ ፈረንሳይኛ የሚያውቅ ሌላ አውሮፓዊ እንዲሾም የሚፈልጉ ነበሩ፡

በዚያን ዘመን አቶ ኃይሉ የአፍሪካ ኮሚቴ አባል ነበር፡፡ እርሱና ሌሎችም አፍሪቃዊ ሊሆን ይገባል በማለታቸው፣ ጉድለቴ ፈረንሳይኛ አለማወቁ ስለሆነ ፈረንሳይኛ እንድማር ተወስነና የአፍሪቃ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች ዋና ጸሐፊ (UBS Regional Secretary for Africa) ተብዬ ተሾምኩ። ብዙ ኃላፊነትን ያዘለ ትልቅ ሹመት ነበር፤ ሥራውን ከመጀመሬ በፊት ለሶስት/አራት ወሮች ወደ ፈረንሳይ አገር ሄጄ ፈረንሳይኛ መማር ነበረብኝ፡፡

ናይሮቢ መኖር እንደ ጀመርኩ ከአገሬው ጋር ለመግባባት እንድችል ሰዋሂሊ ለመማር ወስኜ ትምህርቱን ጀምሬ ነበር፡፡ በመጀመሪያውና ሁለተኛው የሰዋሂሊ ክፍሌ መሐል ፈረንሳይኛ ተማር የሚል ውሳኔ ስለተላለፈብኝ በ42 ዓመት እድሜዬ ፈረንሳይኛ ልማር ወደ ፈረንሳይ አገር ሄድኩ ማለት ነው፡፡ ሻምቦን ሱርሊዮን በምትባል አንዲት ትንሽ ከተማ ወደ ፍራንኮፎን አገሮች ሚሲዮናዊ ሆነው የሚሄዱ የሚማሩበት የፈረንሳይ ቋንቋ ት/ቤት አግኝቼ ወደ እዚያው ሄድሁ። የትምህርቱ መክበድ አይነሳ፤ በዚህ ላይ የቤተሰቤ ናፍቆት አስቸገረኝ፡ ቋንቋን መማር በልጅነት ነው፤ የደነደነው ምላሴ አልገራ አለኝ፡፡ ይህም





ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አማርኛ ሲማሩ የሚያልፉበትን ችግር ይበልጥ እንድረዳ አደረገኝ።

## የአፍሪቃን ማሕበሮች የማገልገል ውጣ ውረድ

አንድ አንድ አገሮች እንዲህና እንዲህ አድርጉ ሲባሉ "የእኛ አገር ልዩ ነች" በማለት ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ያሳያሉ። እራሳቸውን የሚችሉ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች አሉ፡፡ እርዳታ ከውጭ፡- ከዩ.ቢ.ኤስ፣ የሚያስፈልጋቸው አሉ፡፡ ለገንዘቧ ብለው ሳይወዱ በግድ ሃሳብ ወይም ምክር የሚቀበሉም ነበሩ።

ሥራችን መጽሐፍ ቅዱስን ማስተርጎም፣ ማሳተምና ማስራጨት ነበር። የምናስራጨው ሰዎች ሊገዙ በሚችሉበት ዋጋ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ፣ አንደኛ. ክርስቲያኖችና እብያት ክርስቲያናት ገንዘብ እንዲለግሱ ማስድረግ፡፡ ሁለተኛ መጽሐፍ ቅዱስን በተቻለ መጠን በዝቅተኛ ዋጋ የሚታተምበት ቦታ መፈለግ ነበረብን፡፡ ለዚህም ተወዳዳሪ አገሮች ኮሪያና ብራዚል ነበሩ፡፡ የመጓጓዣ ላለመክፈልና ለከብራቸው ሊሉ በሃገራቸው የሚያሳትሙ አሉ፡፡ ይህን ሁሉ ማስተባበር የእኛ ሥራ ነበር።

ብሔራዊ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች የዩ.ቢ.ኤስ አባል ናቸው። ቢሆኑም እራሳቸውን የሚችሉና ገንዘብም የሚያዋጡ እና፣ እራሳቸውን የማይችሉ በሚል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ በአፍሪቃ ራሷን የምትችል መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር የደቡብ አፍሪቃ ብቻ ነበረች፡፡ ሌሎች በአስተዳደር እራሳቸውን የሚችሉ ግን ከዩ.ቢ.ኤስ. በጀት የሚደጎምላቸው ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ከእነዚህ ዉስጥ አንዷ ነበረች። ብሄራዊ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር የሌላቸው አገሮችም ነበሩ።

እኔ የአፍሪቃ ማህበሮች ዋና ጸሃፊ ስሆን በአፍሪቃ ብሄራዊ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ያላቸው ስምንት ነበሩ፡፡ ደቡብ አፍሪቃ፣ ማደጋስካር፣ ኬንያ፣ ኢትዮጵያ፣

ኮንጎ፣ ካሜሩን፣ ናይጄሪያና ጋና ብቻ ነበሩ። እኔ ስለት አስራ ስድስት ሆነው ነበር። ሌሎች አገሮች በነዚህ አማካይነት ወይም በቀጥታ የማስተዳድራቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቢሮዎች የምንላቸው ነበሩ። በዚህ ደረጃ ያሉ ብሄራዊ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር እንዲያቋቁሙ መርዳት አንዱ የትኩረት አቅጣጫዬ ነበር።

ብሄራዊ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች በሚገባ የዩ.ቢ.ኤስን መመሪያ በመከተል ሥራቸውን እንዲሠሩ ማድረግ በጣም ከባድና አስቸጋሪ ነገር ነበር፡፡ እኔን በጣም ያስቸገሩኝ ናይጄሪያና ኢትዮጵያ ናቸው፡፡ ናይጄሪያ ከማነነታቸው የተነሳ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ በተለይ ከአፄ ኃይሉ በኋላ በአወቅሁሽ ናቅሁሽ ምክንያት የተነሳ ነበር። ከኢትዮጵያ ጋር የነበረኝን ንትርክ አላነሳውም። ብሔራዊ ደረጃ ያልደረሱም ቢሆን ያስቸገሩኝ ብዙ ነበሩ። ለምሳሌ በአንድ አገር የነበረው ኃላፊ በሚገባ ሥራውን አይሠራም ነበር፤ ስለዚህም መከርነው፤ ምክራችንን ተቀብሎ በሥራ ላይ ኢያውልም፡፡ ሥልጠና ሰጠነው፤ እንደ ሠለጠነው አይሠራም። ለሁለት አመት ያህል ቻልነው፤ አልሰማንም። ወደ እዚያው ሄድሁና "በስርጭት ጎበዝ ነህ፤ ሆኖም አገርህ አሁንም ብሄራዊ ማህበር አይደሰቺም፡፡ ጎረቤቶችህ አቋቁመው የዩቢኤስ አባል ናቸው፡፡ እናንተ ግን አይደላችሁም፤ ስለዚህ ዋና ጸሀፊ ሊሆን የሚችል ሰው መፈለግ አለብን፤ የስንብት ደብዳቤ አቅርብ" አልኩት። "እኔ ምን ልሆን ነው" ብሎ ቡራ ከረዩ አለ፡፡ በቂ የመሰነባበቻ እንደምከፍለው ስለነገርሁት የስንብት ወረቀቱን አቀረበልኝ።

አንደ እነዚህ ባሉ አገሮችም የመማከርት ጉባኤ አለኝ፡፡ የሰጠኝን የስንብት ወረቀት ይገፔ ሌላ ጸሐፊ እንዲፈልጉ ጠየቅኋቸው፡፡ "ለምን? ከእሉ የሚበልጥ ሰው የለንም" አሉኝ፡፡ ከእነርሱም ጋር ተነታረከሁ፤ እምቢ ማለቴን ሊያዩ "ኮሎኒያሊዝም መልኳን ለውጣ መጣች" አሉ። እኔ ከአገሬ ከኢትዮጵያ ወይም ከአውሮፓ ለአገራችሁ ማህበር ጸሐፊ አመጣለሁ አላልኩም ብያቸው ተለያየን። ከሊቀ መንበሩ ጋር በመጠኑ ስለ ምንግባባ ዋና ጸሐፊ ሊሆን የሚችል መፈለግ ቀጠልን። እንዲህ ያለ ተግዳሮትም ነበረብኝ።





ያንዲት ትንሽ አገር ኃላፊ የፈጠረብኝን አንድ ሌላ ተግዳሮት ልጨምር፡፡ ለውዩው ሊያሳስረኝ ነበር፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው። በዚያ ያሉት ሠራተኞች አራት ነበሩ፡፡ የቢሮ ጸሐፊ፣ ተላላኪ፣ ሱቅ ሺያጭና እርሱ፡፡ የሂሳብ መዝገቡን የሚይዘው እርሱ ነበር፡፡ በያመቱ በሂሳብ መርማሪዎች አስመረመርሁ እያለ ሪፖርት ይልክልናል። በጉብኝቴ ጊዜ ሂሳቡን ስመረምር ለቢሮ ሻይ ያወጣው ወጪ በጣም ብዙ ሆኖ አገኘሁት፡፡ "የስኳር ዋጋ ስንት ቢሆን ነው? ለሻይ ይሄን ያህል የምታወጣው" አልኩት፡፡ "አልፎ አልፎ ኬክም እንበላለን" አለኝ፡፡ እንደዛም ቢሆን ብዙ ነበር የወጣው ወጪ፡፡ አላሳመነኝም፤ ማስረጃም የለም፤ ወደ ኪስ የሄደ ገንዘብ መኖሩን ጠረጠርሁ፡፡ ምርመራዬን ቀጠልሁ፤ በባንክ አለ የተባለውን ገንዘብ ስለተጠራጠርሁ ወደ ባንክ እንሄድ ብዬው ሄድን፡፡ ባንክ ስንደርስ፣ "ለወፍጮ የተበደራችሁትን ሳይጨምር ይሄን ያህል አላችሁ" ተባልሁ፡፡ የምን የወፍጮ ብድር ነው" ስለው በማህበሩ ስም ለግል የወፍጮ ሥራ እንደ ተበደረና እየከፈለ እንዳለ ነገረኝ።

ቢሮ ስንመላለስ ሲላም ጉድለት እንዳለ ለማየት ሞከርሁና፣ እያደርግህ ያለው ልክ አይደለም፤ የስንበት ወረቀት ስጠኝ አልኩት፡፡ እሺ ብሎ ወጣ፤ ቶሎ አልተመለሰም፡፡ ወደ አረፍኩበት ወደ አንድ የካቶሊክ እንግዳ ቤት ለምሳ ሄጄ ምሳዬን በልቼ ብድግ ስል አንድ ሰውዬ ጠጋ ብሎኝ ፓስፖርትህን እፈልጋለሁ አለኝ፡፡ የኢሚግሬሽን ሰው መሆኑንም ገለጸልኝ፡፡ "ለምን?" ስለው "የእምፋቡሳን ጉዳይ ምን ልታደርግ ነው?" አለኝ። "ወደ አገራችሁ ስገባ ፓስፖርቴን አሳይቼአለሁ፤ ስወጣ አሳያለሁ" አልኩት። ቀጥዬም "ፓስፖርቱ የእኔ የሚሊዮን በለጠ ነው፡፡ የእምፋቡሳ ጉዳይ የአፍሪቃ U.B.S. ዋና ጸሐፊ ጉዳይ ነው" አልኩት፡፡ "ያ ሰው አንተ ነህ" እያለ ከእኔ ጋር ሲነታረክ የማረፊያ ቤቱ ኃላፊ አንድ ቤልጂጋዊ መጣና ሊዳኘን ሞከረ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ የፓስፖርቴ ነገር የኢትዮጵያና የመንግስትህ ጉዳይ ይሆናል ብዬው ተለያየን።

ወደ ከፍሌ ሂጄ ባጠያይቅ በአገሩ የኢትዮጵያ ኢምባሲ የለም፡፡ ለግብጽ ኢምባሲ ደወዬ ምክር ጠየቅኹ፡፡ ምክራቸውን ለገሱኝ። በዚያቸም አገር

መማክርት ጉባኤ ነበረኝ:: ወደ ሊቀ መንበሩ ሄጄ ጸሐፊ ተብዬው ሃላፊ እያደረገ ያለውንና የገጠመኝን ሁሉ ነገርሁት:: በጣም አዘነ:: ሰውዬው ትልቅ ሰው ስለነበር የኢሚግሬሽኑ ሰውዬ ጥያቄ ተገቢ እንዳልሆነም ስለ ተረዳ በአስቸኳይ የመማክርቱን ጉባኤ ጠርቶ ጸሐፊው ወዲያው እንዲሰናበት ተደረገ። ሳልታሰርም ከአዛች አገር ወጣሁ።

## የአመራር ሂደት

የአፍሪቃ መ.ቅ. ማሕበሮች ኮሚቴ (AFREC) እኔ የማቅደውን ይመለከታል፣ በረዳቶቼ እገዛ የምተልማቸውን ፕሮግራሞች ያያል፣ ያፀድቅልኝም ነበር:: በተጨማሪም የአፍሪቃን የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ሥራ በበላይ ይመለከታል። ይህ ካሚቴ በአመት ሁለቴ ይሰበሰባል:: አንደኛው ስብስባ ስለጠቅላላ አስተዳደርና ፖሊሲ ሲሆን ሌላው የበጀት ነበር:: ለዚህ ስብሰባ መዘጋጀትና የስብሰባውን ዉሳኔዎች መፈፀምና ማስፈፀም የኔ ሃላፊነት ነበር።

በቢሮዬ ብዙ ረዳቶች አሉኝ፤ የትርጉም አማካሪዎች አስተባባሪ፣ የአስተዳደር፣ የስርጭት፣ የህትመት አማካሪዎች ነበሩኝ። እያንዳንዳቸው ጸሃፊና ረዳቶችም አሏቸው:: በመላው አፍሪቃ በልዩ ልዩ አገሮች የትምህርት ደረጃቸው ዶክተር የሆነ የትርጉም አማካሪዎችም ነበሩኝ:: አብዛኞቹ ፈረንጆች ነበሩ:: የነዚህ ሁሉ አለቃ መሆን ቀላል አልነበርም:: በተለይ የትርጉም አማካሪዎቹ አትቆጣጠረን የሚሉ ነበሩ:: ምን ሲሰሩ እንደሚዉሉ ባላውቅም በያመቱ መጨረሻ ዘገባቸው ሰራቸው እንዲታይ አደረግሁ:: አንድ የትርጉም አማካሪ ለአሰር ያህል ቋንቋዎች ሃላፊ ነው:: እያንዳንዱ ቋንቋ ሁለት/ሶስት ተርጓሚዎች ይኖሩታል:: የሁሉንም ትርጉም አማካሪ ሥራ የሚከታተልና የሚቆጣጠር የትርጉም አማካሪዎች አስተባባሪ (Regional Translation Coordinator) አጠገቤ ነበረ። ከእነርሱ ጋር የነበረኝ ተግዳሮት ቀላል አልነበርም:: ከእነኚህ ከትርጉም አማካሪዎች አንድ ኢትዮጵያዊው ቄስ ዶክተር ምከረ ነበሩ:: በስብሰባ ላይ ምንም አይሉም፤ በውጭ ግን በጣም እንደሚከሩብኝ ይነግሩኝ ነበር።





የአስተዳደር አማካሪዎች ተጠሪነታቸው ለበጀትና ፋይናንስ አስተባባሪው ነው:: በየገሩ ሂሳብ በሥርአት መያዝ ነበረበት:: መጻህፍት እስኪሸጡ በደንብ መያዝ አለባቸው፤ ያሉና የሚሸጡት ቁጥራቸው በማንኛውም ጊዜ መታወቅ አለበት:: ሥራችን የሚለካው በየአመቱ በየአገሩና በመላው አፍሪቃ ስንት ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስንት አዲስ ኪዳን፣ ስንት ወንጌሎች እንደተሰራጩ በመቁጠር ነበር።

የህትመት አማካሪዎች ሃላፊነት በዝቅተኛ ዋጋ የሚታተምበት ቦታ ፈልገው አሳትመው ወደየገሩ እንዲደርስ ማድረግ ነው:: ወንጌሎች የሚታተሙት በያገሩ ስለሆነ በዚህም ጥንቃቄ እንዲደረግ ለያገሩ መ.ቅ.ማ. ምክር ይሰጣሉ። የስርጨት አማካሪዎች የስርጭት ዘዴ እየዞሩ ያስተምራሉ።

እኔ የእነዚህ ሁሉ አለቃ ከመሆንም በላይ በተለይ ትኩረቴ ብሄራዊ መ.ቅ.ማ. ምስረታና እና ካሉት ማህበር ቦርዶችና የየአገሩ ዋና ጸሃፊዎች ጋር መስራት ነበር (በእርግጥ መነታረክ ብል እመርጣለሁ):: የሁሉም አገር ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል እንዲደርሳቸው ያስፈልጋል:: ብሄራዊ መ.ቅ.ማ. ለሌላቸው ቃሉ እንዲደርስ የሚደረገው በጎረቤት አገር አማካይነት ነበር:: ለምሳሌ ኢትዮጵያ ለጂቡቲና ለሱማልያ ሃላፊ ነበረች/ነች:: እኔ የኢትዮጵያ መ.ቅ.ማ ዋና ጸሃፊ በነበርኩበት ጊዜ ወደ እነዚህ ሁለት አገሮች ሄጄ ለነኚህ ህዝቦች ቃሉ እንዲደርስ ለማድረግ ሞክሬአለሁ።

የአፍሪቃ ዋና ጸሐፊነቴ አፍሪቃን እየዞርሁ እንዳይ አድርጎኛል:: በአፍሪቃ ያላየሁዋቸው አገሮች ከሶስት አይበልጡም። አልፎ አልፎም የአፍሪቃ መሪዎች እጅም የመጨበጥ እድል ገጥሞኛል። ለመጥቀስ ያህል የኬንት ካውንዳን እጅ ጨብጫለሁ። ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች አካሂደናል፤ አንዱ ፕሮግራም "መጽሐፍ ቅዱስ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች" የሚል ነበር:: ፕሮግራሙ በየአገሩ ባሉት የመ. ቅ. ማ. የሚዘጋጅ ነበር:: የዛምቢያው ማሕበር ፕሮግራም አዘጋጅቶ ጋብዞኝ ወደ እዚያው ሄጄ ነበር:: በወቅቱ ከፕሬዚደንቱ ድጋፍ ለማግኘት እንድረዳቸው አቅደውት በነበረው ፕሮግራም መሠረት ከካውንዳ ጋር እንድገናኝ አስችሎኛል። ዋና ጸሐፊው ቀጠሮ ሲጠይቋቸው መልካም ነው ለቁርስ ይዘኸው ና ተብሎ አንድ

ቅዳሜ ጠዋት ቢታቸው ሄጄ ነበር፡፡ እጅ መጨበጥ ብቻ ሳይሆን ከርሳቸው ጋር በቤታቸው ቁርስ በልቼአለሁ። ስለ ግርማዊ ጃንሆይም ተጨዋውተናል። በጭውውታችን ወቅትም ግርማዊነታቸው ለአርሳቸው ኬንት ካውንዳ እንደ አባት፣ ታላቅ አማካሪ እንደ ነበሩ ገልጸውልኛል።

## ጉዞዎችና ፈተናቸው

ስለአፍሪቃ ጉዞ ዉጣ ውረዶች የምላቸው ብዙ ቢኖሩም ስለ አንዱ ላውጋ። ከናይሮቢ ቢሮዬ ሰወጣ ሶስት/አራት አገሮች ጎብኝቼ አመለሳለሁ በአንድ ወቅት ወደ አንጎላ መሄድ ነበረብኝ። በዚያን ጊዜ ወደ አንጎላ የሚሄድ የናይጄሪያ አየር መንገድ ብቻ በመሆኑ ወደ አዚያ ሰሄድ የናይጄሪያንና የካሜሩንን መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበሮች ለመጎብኘት አቀድሁ። የጉዞ አቅዴም ከናይሮቢ ተነሰቼ፡- ሌጎስ - ሉዋንዳ አንደገና - ሌጎስ -- ዱዋላ -- ናይሮቢ ነበር፡፡ ከናይሮቢ ወደ ሌጎስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በረርሁ፡፡

የናይጄሪያ ጉዳዬን ጨርሼ በናይጄሪያ አየር መንገድ ከሌጎስ ወደ ሉዋንዳ ሰንበር ዱዋላ ካሜሩን አርፈን መንገደኞች አውርደን ወደ ሉዋንዳ ጉዞ ቀጠልን። ሉዋንዳ ላይ መመለሻዬን ለማመቻቸት ወደ ጓዞ ወኪል ሄድሁ፣ ቲኬቴ ከሉዋንዳ ሌጎስ ቢልም እኔ ቀጥሎ ጉዳይ ያለኝ ካሜሩን ሰለሆነ አይሮፕላኑ ዱዋላ ሰለሚያርፍ ወደ ሌጎስ በመቀጠል ፈንታ ዱዋላ ልውረድ፤ ለካሜሩን ቪዛ አለኝ አልኩት። "የትራፊክ ራይት ስለ ሌላቸው አይቻልም" አለኝ፡፡ "ይህንን መብት የሚሰጠው ማነው? እንዲፈቀደልኝስ የምጠይቀው ሰው የለምን?" አልኩት፡፡ "የሚፈቅደው የአንጎላና የናይጄሪያ ሲቪል አቪዬሽን ሰለሆነ አጠይቃለሁ" ብሎኝ ተለያየን። በማግስቱ ቲኬቴን ለመውሰድ ስመጣ "አልተፈቀደም" አለኝ፡፡ "ለመሆኑ ያልፈቀደው ናይጄሪያ ወይስ የአንጎላ ሲቪል አቪዬሽን ነው?" አልኩት፡፡ "አዝናለሁ አንጎላ ነው" አለኝ፡፡ "እንግዲህ እንዲህ ከሆነ ስመለስ ከመንገደኛ አስተናጋጆች (ሆስቴስ) ጋር አወዳጅና ድዋላ ላይ እንዲያወርዱኝ እጠይቃቸዋለሁ" አልኩት፡፡





" የሚቻል አይመስለኝም" አለኝ።

እንዳቀድኩት ወደ ዱዋላ ስንበር ከሆስቴሶቹ ጋር መጫወት ጀመርሁ፡፡ ተወዳጀሁና "አሁን ወደ ሌጎስ የምሄድበት ምንም ምክንያት የለኝም፤ ብሄድም ነገ ጠዋት መመለስ አለብኝ፤ ስለዚህ አይሮፕላኑ ዱዋላ ሲያርፍ እኔም ልውረድ" አልኳቸው፡፡ "አይ! አይቻልም" ብለው በአንድ ጊዜ ጭውዉታቸውን አቆሙና ትተውኝ ሄዱ።

ዱዋላ ስንደርስ ሆስቴሶቹን "ካፒቴኑን ላናግር እፈልጋለሁ" አልኳቸው፡፡ መልስ ሳይሰጡኝ ትተውኝ ሄዱ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የናይጄሪያ አየር መንገድ የዱዋላ አየር ማረፊያ ሃላፊ አውሮፕላኑ ላይ ወጥቶ ስለነበር ጥያቄህን ለእርሱ አቅርብ አሉኝ፡፡ ጥያቄን አቀርብሁ፤ በቁጣ መልክ "አይቻልም" አለኝ፡፡ እኔ በጥሞና ቲኬቴን እያሳየሁ "አሁን ወደ ሌጎስ ብትወስዱኝ ነገ መመለስ አለብኝ፤ ገንዘብ ይመለሰልኝ አልልም፤ ቪዛ አለኝ፤ ልውረድ" ስል፡ አሁንም በቁጣ አይቻልም አለኝ፡፡ እኔም በቁጣ፡ "ለምን!" አልኩት፡፡ "የአንጎላ መንግስት አይፈቅድልህም" አለኝ፡፡ "እንዴ፡ ያለነው ካሜሩን ነው፤ ይህ የናይጄሪያ አየር መንገድ ነው፤ አንጎላ እዚህ ምን አገባው" አልኩትና አወጣለሁ ስለው የሚለውን አጣ። የጅ ቦርሳየን ይዤ ልወጣ ስል "ሻንጣህንም እንሰጥሃለን" ብለው ሰጡኝና ወረደሁ። ያለ ችግር ካሜሩን ገባሁ። በሚቀጥለው ጊዜ ሉዋንዳ ስሄድ የአንጎላ መንግስት አስታውሶ ይይዘኝ ይሆን ብዬ ፈርቼ ነበር። ከሁለት አመት በኋላ ሰመለስ ብዙ ነገሮች ተለውውጠዋል። የኔን በደል የሚያስታውሱበት ምንም መንገድም አልነበረም።

## ከሌሎች UBS መሪዎች ጋር የተደረጉ ስብሰባዎች

የአፍሪቃ ዋና ጸሐፊ ሳለሁ የነበረብኝ ኃላፊነት እንደኔው የክፍለ ዓለም ዋና ጸሐፊዎች ከሆኑትና ከሶሰቱ አለማቀፍ የዩ.ቢ.ኤስ. ባለስልጣናት ጋር በመሆን ለመላው አለም የእግዚአብሔር ቃል እንዲደርስ ማድረግ ነበር፡፡ ይህን ሃላፊነታችንን ለመወጣት በደብዳቤ ከምናደርገው ግንኙነት በተጨማሪ በአመት



አራቱ የዩ.ቢ.ኤስ የስያ፣ አፍሪካ፣ አሜሪካ እና አውሮፓ ዋና ጸሃፊዎች

ሁለቱ መደበኛ ስብሰባ ነበረን። አንደኛው የበጀት ስብሰባ ሲሆን በሎንዶን ወይም ኒውዮርክ ይካሄዳል፡፡

ሁለተኛው በፈረቃ በየክፍለ ዓለማቱ የሚደረገው ነበር። የአፍሪቃ ተራ ሲሆን የምንሰበሰበው በናይሮቢ. አንዳንዴ ደግሞ በተለያዩ የአፍሪካ ዋና ዋና ከተሞች ነበር። የሌሎች ክፍለ ዓለማትም ተራ ሲደርስ እንዲሁ የተለያዩ ቦታዎች እንሰበሰብ ነበር፡፡ ለምሳሌ አንድ ጊዜ በኢየሩሳሌም ተሰብስበን ነበር። እነኚህ ስብሰባዎች አብዛኛውን የአለምን ክፍል እንድናይ አድርጎናል። ጉብኝቱ ከአገልግሎት በረከታችን በተጨማሪ የሆነልን ሌላ በረከት ነበር!! ስለ ኢየሩሳሌሙ ጉዞ ላውራ።

ብዙ ጊዜ ለስብሰባ ወደ አንድ አገር ስንሄድ አገሩን የማየት ሃሳብ የለንም። ትኩረታችን ስብሰባው መቼ ይጀምራል? መቼ ያልቃል? የሚለው ላይ ስለነበር ትኬታችንንም በዚሁ ፕሮግራም መሠረት እናስቆርጣለን፡፡ አንድ አገር ስንደርስ መጀመሪያ የምናደርገው መመለሻችንን ማመቻቸት ነበር። አገሩን ሳናይ እንመለሳለን። ወደ ኢየሩሳለም ስንሄድ ግን ስብሰባው ከመጀመሩ ሁለት ቀን ቀደም ብለን እንድንደርስና ያቺን ቅድስት አገር እንጎበኝ ተባባልን።

ወደ እስራኤል የሚወስዱኝ ብዙ እየር መንገዶች አልነበሩም፡፡ እኔ በኤል አል (የእስራኤል አየር መንገድ) ለመጓዝ ተመዝግብሁ፡፡ ይህም ሶስት ቀን ቀደም አድርጎ ያደርሰኝ ነበር፡፡ በኤል አል መጓዝ ቁጥጥሩ በጣም ከባድ ነበር፡፡ ሻንጣችንን ከፍተን እስመርምረናል፤ የእጅ ቦርሳችንም በደንብ ተመርምሮ ነበር የተሳፈርነው። የእጅ ቦርሳችን ከኛ እንዳይለይም እስጠንቅቀውን ነበር። ቴላቪቭ ስንደርስ እኛም ፓስፖርታችን ላይ እንዳያትሙ ነገርናቸው። እስራኤል የሄደ ሰው አረብ አገር ሲሄድ አይችልም ነበርና።

እኔ አንድ ቀን ቀደም ብዬ በመድረሴ ተጨማሪ ቦታዎችንና የኢትዮጵያን ገዳም ጎበኘሁ። ከኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ጋርም ተዋወቅሁ። በማግስቱ ከጓደኞቼ ጋር ጉብኝት ጀመርን፡፡ መጀመሪያ ወደ ምእራብ ተጉዘን ፍልስጥኤማውያንና እስራኤል የሚነታርኩበትን ከተማ ጋዛን ጎበኘን፡፡ ከተማዋ መርካቶ ብጤ ነበረች፡፡ መኪናችንን እቁመን ዞርዞር ብለን ተመለስን፡፡ ከዚያም ወደ አሽዶድ ተጓዝን፤ አሽዶድ ስንደርስ አንዷት ቦታ እረፍ አልንና አንዷት መጠለያ ስር ለመዝናናት ቁጭ ብለን የያዝነውን ሳንድዊች ለመብላት በየግላችን መዘጋጀት ጀመርን። የምንጓዝባትን መኪና እቃ ማስቀመጫ ስከፍት ቦርሳዬ የለቺም፤ ከው ብዬ ደነገጥኩ፤ ዉስጧ ሳንድዊቼ ብቻ ሳይሆን ፓስፖርቴና ገንዘቤ (travellers cheque)፣ አንድ ሌሊት ዉጭ ስለምናድር መለወጫ ልብሴ አብሮ ነበር፡፡ ተዘርፏል፡፡ ጋዛ ላይ መኪናችንን ከፍተው ወስደውታል ማለት ነው። በእስራኤል የኢትዮጵያ ኢምባሲ የለም፤ ምን ላድርግ? መዘረፌን ለፖሊስ አመልከትኩና፣ ፖሊስ ፓስፖርቴ መጥፋቱን የሚገልጽ ብጣሽ ወረቀት ሰጥቶኝ ጉዞአችንን (ወደ ሰሜን) ቀጠልን፡፡ የምንጓዘው በብርቱካን ዛፎች እርሻ መሃል ነበር፡፡ ቆም እያልን እርሻው ዉስጥ ገብተን ብርቱካን እየቀጠፍን በላን፤ በእስራኤል ህግ አዛው እርሻ ውስጥ ሆኖ ቆርጦ መብላት ይፈቀዳል ይዞ መሄድ ግን አይቻልም።

ናዝሬት አደርን፤ ኢየሱስ ያደገባት ቦታ ላይ ታላቅ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቷል፡፡ ተራራማ ቦታ ነበረች፤ እየተዟዟርን ጎበኘን ኢየሱስ እዚህ ሜዳ ተጫውቶ ነበር፣ በዚህ መንገድ ሄዶ ነበር፤. . ወዘተ እያልን ገመትን። ያረፍነው አንድ እንግዳ ማረፊያ ቤት ነበር፡፡

በማግስቱ አቀበቷን ወጣ ብለን አሽቆልቁለን፤ ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ ወረድንና ቅፍርናሆም ከተማ ቆምን። የጴጥሮስ አማች ቤት እዚህ ነበር ብለው አሳዩን። ያችን ትንሽ ከተማ ከጎበኘን በኋላ የጥብርያዶስን ባሕር በቀኛችን እያየን ጉዞ ወደ ታች ቀጠልን፡፡ ከጥቂት ኪሎሜትር በኋላ በቀኛችን የዮርዳኖስ ወንዝ አየን፡፡ ዮሐንስ ኢየሱስን ያጠመቀበት ቦታ ይህ ነው ተባልን፡፡ ከመኪናችን ወረድን፤ እኔና የአሜሪካ መ. ቅ. ማ. ዋና ጸሐፊ ጫማችንን አወለቅንና ዮርዳኖስ ውስጥ ገብተን አንዳችን አንዳችንን ለማጥመቅ ሙከራ አደረግን (ታዲያ በመድፈቅ አልነበረም!)፡፡ ጉዞአችንን ወደ ታች ስንቀጥል አንዲት አውቶቡስ ላይ 'ኢያሪኮ' የሚል ጽሁፍ አየሁ። ወደ ኢያሪኮ ከተማ እየሄድን ነበር። ከተማዋን በግራችን እያየን ቀጠልንና ጭንጫ መሬት ላይ ተጉዘን ኢየሩሳሌም ገባን፡፡ አብዛኛው የእስራኤል መሬት እንደዚህ ያለ ጭንጫ ነው ተብሎ ተነገረን፡፡ እንዲህ ባለው መሬት ላይ ዘርተው እንዴት ብዙ እንደሚያመርቱ ገረመን።

በማግስቱ ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት መጀመሪያ ወደ አሜሪካን ኢክስፕረስ ሂጄ የጉዞ ቼኮቼ እንደጠፉብኝ ነገርኳቸው፡፡ ግድየለም ሌላ እንሰጥሃለን ብለው ፎርም አስሞሉኝ፡፡ ስንት ዶላር እንደጠፋብኝ ጠይቀው ሊሰጡኝ መታወቂያ እንዳሳያቸው ጠየቁኝ፤ ፓስፖርቴ ጠፍቷል፤ የመኪና መንጃ ፈቃድ፤ ወይም እኔን የሚገልጽ ፎቶ ግራፍ ያለበት ማንኛውም አይነት መታወቂያ እንዳለኝ ጠየቁኝ፡፡ ምንም አልነበረኝም "ሁሉም ተዘርፏል" አልኳቸው፡፡

እናዝናለን ልንሰጥህ አንችልም ብለው አሰናበቱኝ። የመታወቂያ ወረቀትን አስፈላጊነት ተረዳሁ፡፡ ለካ ማንነታችንን የሚገልጸው ይዘነው የምንሄደው ወረቀት ነበር፡፡ እንዲህ ያለ ወረቀት በእስራኤል አገር ማን ሊሰጠኝ ይችላል ብዬ ሳስብ የኦርቶዶክሱ ሊቀ ጳጳስ ወደ አእምሮዬ መጡልኝ፡፡ እርሳቸው ሊሰጡኝ እንደሚችሉ አሰብሁ፡፡ ወደ እርሳቸው ሄድሁና ፓስፖርቴ በመጥፋቱ ተቸግሬአለሁና እባክዎ "ይህን ወረቀት የያዘው ሚሊዮን በለጠ ነው" የምትል አንዲት መታወቂያ ወረቀት ስጡኝ አልኳቸው፡፡ "ይህን ወረቀት የያዘው ሚሊዮን በለጠ ነኝ የሚል ወረቀት ይሰጠኝ ስላለ ይህን ሰጥተነዋል" የሚል ሰጡኝ። ሊጠቅመኝ የሚችል አልነበረም።





ናይሮቢ ደወልሁና ግደይ ከኢትዮጵያ ኢምባሲ ሌሴ ፓሴ አውጥታ እንድትልክልኝ አድርጌ ተላከልኝ። የእስራኤል መንግስትም ሌሴ ፓሴ ሰጥቶኝ ስለነበር ከአገራቸው በሰላም መውጣት ቻልሁ። ሆኖም ሰወጣ አንዲት ትንሽ አስቂኝ ነገር ተከስታ ነበር። ማንኛውም ሰው ወደ እስራኤል ሲገባ አንዲት ትንሽ ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ ያቺ የተሰጠችኝ ወረቀት ከነፓስፖርቴ ተወስዳለች፤ ልወጣ ስል የኢሚግሬሽኗ ሴት የእስራኤል መንግስት የሰጠኝን ሌሴ ፓሴ ሰጥቼ ልታትምበት ስትዘጋጅ "ስትገባ የተሰጠህ ወረቀት የት አለ?" አለቺኝ፡፡ "ተሰረቀብኝ" አልኳት፤ "ማን ሰረቀው?" ስትለኝ፡ በልቤ "እንዴት ያለ ጥያቄ ነው ማን ሊሰርቀኝ ይችላል ታዲያ" እያልኩ "ሌባ" የምትል ልሙጥ መልስ ሰጠኋት። አጠገቧ ያለው ረዳትዋ ሳቀ፤ እኔም ሳቅሁ። ተሳስቀን ተለያየን። በጉዞዬ ይህም ገጥሞኝ ነበር።

## ኑሮና አገልግሎት በናይሮቢ

ናይሮቢ እንደገባን ማምለክ የጀመርነው በናይሮቢ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ በናይሮቢ የነበርን ጥቂት ወንድሞች፡ (አቶ ሙላቱ በላቸውና አሸናፊ ዘውገ፥ እኔ) ቅዳሜ ቅዳሜ ጠዋት እየተገናኘን ለኢትዮጵያ እንጸልይ ነበር፡፡ ከኢትዮጵያ ሰዎች ሲመጡ በሃገር ቤት ስለሚሆነው እንጠይቃለን፣ እናዝናለን፣ እንቆዝማለን ጌታ የሚሰራቸውን ታምራቶችም እንሰማለን። ከአንድ ወንድም የሰማነው የማልረሳው ነበር፡፡

ሶስት ወንድሞች በአንዱ ቤት ሲጸልዩ አመሹና ጸሎታቸውን ሲያቆሙ ሰዓታቸውን ሲያዩ ሰአት እላፊ ሆኗል፡፡ የአንዱ ቤት እዛው ሰፈር ስለሆነ ሊሄድ ወሰነና ወጣ። እርሱ እንደ ወጣ የቀሩት ሁለቱ በግንባራቸው ተደፍተው "ጌታ ሆይ የአብዮት ጠባቂዎች እንዳይይዙት ጠብቀው" እያሉ ጸለዩ፤ ወደቤቱ እየሄደ እያለ የአብዮት ጠባቂዎች በመንገዱ ሌላኛው በኩል ሲሄዱ አያቸው፣ እነርሱም አዩት፤ ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዴት አመሻችሁ እያለ መንገዱን ቀጠለ በሰላም ወደ ቤቱ ገባ።

በማግስቱ ከቤቱ ወጥቶ ጓደኞቹን ሲያቸው ሲመለስ የአብዮት ጠባቂዎቹን በመንገድ ላይ ያገኛቸዋል:: ትላንትና ማታ መሳሪያ ይዘው በጎንህ የሚሄዱት ሁለት ሰዎች እነማን ነበሩ? አሉት:: ሰውየው ግራ ተጋብቶ "እረ ማንም አልነበረም" አላቸው። "እንዴ የሚሸኙህ ሰዎች እንደ ነበሩ እኛ አይተናል" ብለው ተከራከሩት። ጓደኞቹ ቤት ሲደርስ ማታ ደህና እንደ ደረሰ ነገር ግን አሁን ሲመለስ ከአብዮት ጠባቂዎቹ ጋር የነበረውን ውይይት ነገራቸው። ሁለቱ በጎኑ የነበሩት በጸሎት ላይ የነበሩት ጓደኞቹ እንደ ነበሩ ተረዱ። እንደዚህ ያሉ ብዙ ታሪኮችን እንሰማ ነበር።

ናይሮቢ በገባን ጊዜ ሜኖናይቶች የእሁድ አገልግሎት በኢሰሊ ለመጀመር እየሞከሩ ነበር:: ይህን ይመራ የነበረው ከሱማሊያ ከተባረሩት ሚሲዮኖች አንዱ ዴቪድ ሻንክ የሚባለው ነበር:: በዚያን ጊዜ ብዙ የኢትዮጵያና ሱማሌ ስደተኞች ይገኙ ነበር:: ዴቪድ ሻንክ እነርሱን በወንጌል ለመድረስ እየተጣጣረ ነበር:: የኢስሊን ሜኖኒይት ፌሎውሺፕ ሴንተር እንድትቋቋም ያደረገው እርሱ ነው:: እርሱን ቀድሞ ስለማውቀው በዚህ ሥራው እረዳው ነበር:: የህንጻው ግንባታ ሲያልቅ መደበኛ የሜኖኒይት ቤተ ክርስቲያን አምልኮ እዚያው ውስጥ ተጀመረ። በመሆኑም መጀመሪያ አማኑኤልና ሩት በኋላም ጌድዮናን ሄኖክ የውሃ ጥምቀት የተቀበሉት እዚያ ነበር። ይህን ሁሉ ባደርግም ከእንግድነት ስሜት አልወጣሁም ነበር።

## በናይሮቢ በአማርኛ የአምልኮ መጀመር

በ1972 ዓ.ም በናይሮቢ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ያቀፈ የጌታ ልደት ፕሮግራም አካሄድን:: ሁለት የገና በዓል ለምን ያስፈልጋል የሚለውን ለልጆቻችን ለመመለስ ሞከርን:: የገና በዓል በቀን መቁጠሪያችን መሰረት የሚከበር መሆኑን አስረዳን:: ልጆች በተከለታተሬ ምላሳቸው የልደት ጥቅሶች እንዲሉ አደረግን። እኔም የልደት መልእክት አቀረብሁ:: ህዝቡን ድፎ ዳቦ ጋበዝን፤ ለብዙ ዘመን ኢትዮጵያ የኖረች፣ በዴይስታር ኮሌጅ የምታስተምር እንግሊዛዊት እህት "ያገር ባህል ልብስ ለብሰህ ወዲያና ወዲህ ስትል ሳይህ እንባዬ መጣ" በማለት የዚያን ቀን ስሜቷን ገለጠቺው። ያን ፕሮግራም ማካሄዳችን በናይሮቢ ቋሚ የእሁድ የአምልኮ ፕሮግራም እንድንጀምር አደፋፈረን። በናይሮቢ የምንኖር ከመካነየሱስ፣ ቃለሕይወት፣ መሰረተ ክርስቶስ፣ ሙሉወንጌል ቤተክርስቲያን የመጣን ሁላችንም የየራሳችንን አስተምህሮ ጠብቀን ኅብረት አቋቋምን። ኦርቶዶክሳውያንንና ካቶሊካውያንንም ለማቀፍ ተሞከሯል። ኅብረቷ የምትመራው በየሁለት አመት በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች ነው። ሽማግሌዎቹ በየእሁዱ ቃል በማካፈል ያገለግላሉ። ከጊዜ በኋላ የሚረዳን አገልጋይም አስማራን:: የመጀመሪያው አገልጋያችን ወንድም ተሾመ የሚባል ሲሆን፣ በኋላ ለብዙ ጊዜ ያገለገለን እሳየሽኝ በርኸ ነበር።

የናይሮቢዋ ኅብረታችን አባላት አብዛኛዎቹ ስደተኞች ነበሩ:: ነገር ግን እራሷን ችላ ከማስተዳደሯም በላይ ኢሰሊና ካሪዮባንጊ በሚባሉ ሁለት ቦታዎች የአምልኮ ጊዜ ነበራት:: ኢስሊዎች በመቶ ዘጠና ዘጠኙ ስደተኞች ሲሆኑ ካሪዮባንጊዎች ከደቡብ ኤትዮጵያ ወደ ከንያ መጥተው መኖሪያቸውን ኬንያ ያደረጉ ናቸው። ከጊዜ በሁዋላ በእነኚህ ቦታዎች የሚካሄደው አገልግሎት ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያንነት አደጓል። በኬንያ ዉስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ የስደተኞች ካምፕ እንጎበኝና እይዞአችሁ እንልም ነበር:: በዚህ የጉብኝት አገልግሎትም ተካፍያለሁ።

የናይሮቢ ኅብረት ለብዙ ስደተኞች በረከት በመሆኗ ወደ አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ አሜሪካ ሲሄዱ በሄዱበት ቦታ ከተካፋይነት አልፈው አገልጋዮች የሆኑም አሉ:: በየቦታው የተበታተኑትን ሳያቸው በናይሮቢ በነበሩበት ጊዜ ያቺ ኅብረት ብዙዎችን ትዳር እንዲይዙ ማድረጓን አስተውያለሁ:: በሄዱበት አገር ሳገኛቸው በጣም እንደተረዱና እንደተባረኩ፣ ሲሸኙም የተደረግላቸውን ጸሎት እንደሚያስታውሱ ይነግሩኛል። ስንሸኛቸው "እግዚአብሔር ከፊት ሆኖ ይመራችኋል፣ የእስራኤል አምላክ ከኋላ ሆኖ ይጠብቃችኋል" (ኢሳይ. 52፥12) የምትለዋን የተስፋ ቃል እንሰጣቸው ነበር።

በአመት ሁለቴ የመነቃቂያ ፕሮግራሞች (ኮንፈረንስ) እናካሂዳለን፡፡ አገልጋዮች ከኢትዮጵያ እናስመጣለን፡፡ ዋናው ፕሮግራማችን ለሶስት ቀን፣ ዓርብ እስከ እሁድ ሲሆን ሊያገለግሉን የሚመጡትን ከቤት ወደ ቤት እየሄዱ እንዲያጽናኑና እንዲያገልግሉን እናደርግ ነበር። በየቤቱም የሚደረግላቸው ግብዣ ራሱን የቻለ መለስተኛ የመነቃቂያ ፕሮግራም ነበር። አገልጋዮች በአመት አንዴ ከናይሮቢ ወጣ ብለን የምንቆይበት የጥሞና ጊዜም ነበረን፡፡ ከናይሮቢ አገልጋዮች እንጋብዝና ያገለግሉንና ያስተምሩን ነበር።

በአንዱ አመት ለነበረን የጥሞና ጊዜ "ለምን ከውጭ ሰው እንጋብዛለን? እርስ በእርሳችን እንማማር" ተባባልንና ወንድም ብርሃኑ ደረሰና እኔ ቃል እንድናካፍል ተደረገ። እኔ ያን ጊዜ ያስተማርኩትን አላስታውስም፤ ግን ብርሃኑ ያለው የማልረሳው ጥሩ መመሪያ የሰጠኝ ነበር። ብርሃኑ እንዲህ አለን "አገልጋዮች እንደ መሆናችን ከባድ ጥያቄ እራሳችንን መጠየቅ አለብን"። ወደ ጥቁር ሰሌዳው አመለከተንና ለእነኚህ ጥያቄዎች መልስ ስጡ አለን።

"እድሜህ/ሽ ስንት ነው?

እስከ ስንት አመት የምትኖር ይመስልሃል/ ይመስልሻል? ከአሁን እስከ እዚያ ምን ልታደርግ ተፈልጋለህ/ ትፈልጊያለሽ?

ምን አገር ልታይ ትፈልጋለህ/ትፈልጊያለሽ?

እህቶች እድሜ መናገር አትወዱ ይሆናል፤

ቢሆንም በፈቃደኝነት እድርጉት"፡፡

ማሰብ ጀመርሁ፤ ያኔ እድሜዬ 57 ነበር፤ እስከ 70 ዓመት አልሁና ስቀንስ 13 ሆነብኝ፤ ደነገጥሁ፤ 80 አልኩና አሁንም 23! ይህም አሳሰበኝ፤ ይህ ሁሉ የሆነው ከመቅጽበት ነበር።

ከኋላዬ ዶክተር ዓለሙ ማሞ ተነሳና፦ "እድሜዬ 35 ነው፤ እስከ 70 ለመኖር እፈልጋለሁ፤ በእለኝ ሙያ ጌታዬን ሳገለግል እንድቆይ እፈልጋለሁ አለ፤ ሩቅ ምስራቅን ለመጎብኘት እፈልጋለሁ" አለ።





እንደገና ከኋላዬ ዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ ተነሳና፦ "እድሜዬ 35 ነው፣ እስከ 70 ዓመት ለመኖር እፈልጋለሁ፤ ጌታን እያገለገልሁ ልኖር እፈልጋለሁ፤ ሩቅ ምስራቅን ለመጎብኘት እፈልጋለሁ" አለ።

ከራሴ ጋር መነጋገር ጀመርሁ፤ "እነኚህ ሁለት ወጣቶች የምኖረው እስከ 70 አመት ነው ሲሉ፣ እኔ 70 የማልልበት ምክንያት ምንድነው?"፡፡ "ጌታ ሆይ እንኳን 70 ዓመት ነገም ልትወስደኝ ትችላለህ፤ 13 አመት አነሰኝ የምልበት ምንም ምክንያት የለኝም፤ ይቅር በለኝ፤ ሌሎችን ግብ አውጥታችሁ ያን ለመፈጸም ትጉ እያልሁ አስተምራለሁ፤ እድሜዬ እስከ 70 ነው ብዬ ያለኝ 13-12-11 ዓመት ነው እያልሁ እኖራለሁ፤ ከዚያ በላይ ብኖር እንደጭማሪ እቆጥራለሁ" አልኩ።

እንደዚህ እያሰብሁ መኖር ትልቅ እረፍት ነው። ለዚህ ትውስታዬ ይህን ምዕራፍ ስጽፍ እድሜዬ 81 አልፎታል፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ስለ ዚያች የጥሞና ቀን ከወንድም ብርሃኑ ጋር ስንጫወት እርሱ ለእራሱ ያስቀመጠው እድሜ 90 መሆኑን ነገረኝ፤ እኔም የአገልግሎት ዘመኔን ወደ 90 ከፍ አድርጌዋለሁ የ20 አመት ጭማሪ ማለት ነው፤ እርሱ ምን ይሳነዋል?፡፡ እርሱ ከጠየቅነው በላይ የሚሰጥ አምላክ ነው። አሁን የሚያሳስበኝ የእድሜዬ መርዘም ሳይሆን፣ ቢሊ ግራሃም እንዳሉት አማሟቴ ነው። የኔ ምኞት በዚህች ምድር እስካለሁ ድረስ የምጠቅም ሰው እንድሆን ነው።

የናይሮቢ ኅብረታችን እራሷን ችላ የምትተዳደር እንደአቅሟ ወንጌል የምታስፋጭም ነበረች፡፡ በያመቱ በጀት እናወጣለን፤ ለምእመኑ እናቀርባለን፤ በጀቱ በአመቱ ዉስጥ ምን ለማድረግ እንዳቀድንም ያሳያል፡፡ በአመት በየሶስት ወር ለምእመኑ ሪፖርት ይቀርባል፡፡ ምእመኖቻችን አብዛኛው ስደተኞች እና ተማሪዎች በመሆናቸው ደሞዝተኞች ጥቂቶች ነበሩ፡፡ ሥራ ያለን ያወጣነውን በጀት እያየን በአመት ዉስጥ ምን ያህል እንደምንሰጥ ቃል እንገባለን፡፡ በገባነው ቃል መሰረት በየወሩ እንሰጣለን፤ በተጨማሪ በየእሁዱ መባ ይሰበሰባል። ኅብረቷ ከምታገኘው አስራት መክፈል አለባት ብለን ያን አስራት ለሌላ ድርጅት ወይም ክርስቲያናዊ አገልግሎት እንሰጥም ነበር። በየሰፈሩም በሳምንቱ መሃል

በየቤተሰቡ የሚካሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ጊዜ ነበረን። ይህ ሁሉ ሕይወታችንን የገነባ ነበር፤ እኔና ግደይ የናይሮቢ ኑሮአችንን ስናስብ ጥሩ መግባባት ላይ የደረስንበት ነበር እንላለን።

## የኢትዮጵያውያን ኮሚዩኒቲ በኬንያ

ናይሮቢ ስንኖር ሌላው የተሳተለፍኩት በኬንያ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር ምስረታ ነበር:: እኛ ከመጀምሪያዎቹ መስራቾች ውስጥ ነበርን:: ናይሮቢ መኖር ስንጀምር ያኔ ኬንያ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ በኢምባሲውና በኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚሰሩ ነበሩ:: አቶ ሽፈራው ቢተው የሚባል በI.B.M የሚሰራ ወንድምም ነበር:: በመጀመሪያው የትንሳኤ በዓል ቀን (1967 ዓ. ም.) ከየቤታችን ወደ ኤምባሲያችን ምግብ ይዘን ሄደን አብረን በመብላት በዓሉን ስናከብር የበዛን መስሎን የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ልናቋቁም ይገባል ብለን ቀለድን።

ቀስ በቀስ በኬንያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እየበዛን ሄድን፤ አንዳንድ ድርጅቶች ድርጅታቸውን ከኢትዮጵያ እየነቀሉ ወደ ኬንያ አመጡ:: አንዱ ድርጅት የምስራቅ አፍሪቃ የአንበጣ መከላከያ ድርጅት ነው። ከጥቂት አመት በኋላ ያገር ቤቱም ፖለቲካ እየተፋፋመ ሲሄድ ኤምባሲያችንም መንቀሳቀስ ጀመረ። አንድ ቀን አምባሳደሩ በናይሮቢ የምንኖረውን ሰበሰቡና በማህበር ልትደራጁ ይገባችኋል አሉን። በመጀመሪያ አላማቸው አልገባንም ነበር፤ በኋላ ስንገምት ግን ለፖለቲካቸው ሊጠቀሙብን ፈልገው ነው አልን። በከተማው ልዩ ልዩ ኮሙኒቲዎች ስለነበሩ በነገሩ ተስማማን:: "እንግዲህ የመጀመሪያው ነገር መተዳደሪያ ደንብ ልናወጣ ይገባል፤ በዚያም ዉስጥ የኮሙኒቲው አላማዎች መገለጽ ይገባቸዋል" የሚል ሃሰብ ሰነዘርሁ::

በነገሩ ተጨማሪ ውይይት ተደረገና መተዳደሪያ ደንቡን የሚያረቁ ሰዎች ይመረጡ ተብሎ ከኢምባሲ ዶክተር ስርጹ፤ አቶ ተሻለ ከአንበጣ መከላከያ ድረጅት ሃላፊ፤ እኔና ሁለት ሌሎች ተመረጥን:: አምስታችን ባደረግነው የመጀመሪያ ስብሰባ እኔን ሰብሳቢ አደረጉኝ። የሰብሰባችን የመጀመሪያው አጀንዳ ለድርጅታችን መጠሪያ ስም ማውጣት በመሆኑ፤ 'የኢትዮጲያ ኮሙኒቲ' እንበል ስል "እይ ኢትዮጵያ ብቻ የሚለው አይበቃም፤ የጊዜውን ኢትዮጵያ የሚገልጽ መሆን አለበት ተባለ:: የጊዜውን ፖለቲካ መግለጽ አያስፈለገውም የሚል ሃሳብ ተነሳና ሳንስማማ ተለያየን። የሚቋቋመውን ማኅበር ለፖለቲካ ጥቅም እንደ ተፈለገ ሊበልጥ እየገባን ሂደ። እጅ ሳንሰጥ መተዳደሪያ ደንቡን ማውጣት ቀጠልን።

የማህበሩ አባል ማን ሊሆን እንደሚችል ስንነጋገር፣ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያን የሚወድ አልን:: በስመ ኢትዮጵያ ማንኛውም ሊሆን አይችልም የሚል ሃሳብ ተንጸባረቀ:: ሰደተኞች እንዳይገቡ ስለተፈለገ በኢምባሲው የተመዘገበ መሆን አለበት ሲባል ደንብ ማውጣቱ እዚህ ላይ ቆመ። ካውንስለሩም ነድቶ ከበለለ፤ አባል ጎደለ በሚል የደንቡን ነገር ቸል ብንለውም ለሌላም ጉዳይ ኮሚቴው ተጠሪ ሆነ:: አባላቱ ተለዋወጡ፤ እኔ ግን ልተወው አልቻልኩም:: ያገር ቤቱም ፖለቲካ እየተጧጧፈ ሄደ::

የአስረኛው ኢ.ሰ.ፓ. በአል ሊሆን ሲል ረዘም ላለ ጊዜ ከናይሮቢ ለመውጣት ምክትሉን አንድ ጥያቄ ጠየቅሁት:: "ስለዚህ አስረኛ የኢ.ሳ.ፓ. በአል እስካሁን አምባሳደሩ ምንም አላሉንም፤ እኔ አልኖርም፤ በዓል አዘጋጁ ቢሉ ምን መልስ ትሰጣለህ?" አልኩት:: ደነገጠ፤ "ምን ልል እችላለሁ? ምን ላደርግ ነው?" አለኝ፤ "እኔ ብኖር የምለው፡ 'የኛ ማህበር ትኩረት በሕዝባዊና በባህላዊ ጉዳዮች ላይ ነው፤ ይህ ያገር ፖለቲካ ጉዳይ ስለሆነ ይህን በዓል ማዘጋጀት ያለበት ኢምባሲው ነው' አላቸዋለሁ" አልኩት:: በጣም ደስ አለው፤ ያልኩት አልቀረም፤ ተጠየቀና ይህን መልስ በመስጠቱ በዓሉን ኢምባሲው አዘጋጀ። የቀድሞው አምባሳደራችን ጡረታ ወጥተው ሲሄዱ አዲሱ የተሾሙት በማህበሩ ምስረታ እንድንገፋ አሳሰቡን:: ቀድሞ ያጣላን የስደተኞች ነገር ስለሆነ "ማንኛውም በህጋዊ ፈቃድ (Bona fide Resident Ethiopian) አባል ሊሆን ይችላል ብለን መተዳደሪያ ደንቡን በእንግሊዝኛ አዘጋጅተን በነገሩ ገፋንበት:: በኬንያ መንግስት እውቅና አገኘን:: መተዳደሪያ ደንቡን ወደ አማርኛ ተርጉመን ሰዎች አባል እንዲሆኑ

ጋበዝን፡፡ አባል ለመሆን የላክነውን ፎርም ሞልተው የመለሱትን ለምስረታ ፕሮግራም ጠራን። በዚህ ፕሮግራም ላይ ትልቁ አጀንዳ ለማህበራችን ሹማምንት መምረጥ ነበር፡፡ እስካሁን የሥራሁት ይበቃል ብልም የማህበሩ ሊቀመንበር እንድሆን መረጡኝ።

የማህበሩ አንዱ አላማ በበጎ አድራጎት ሥራ መሳተፍ ስለሆነ ፕሮጀችቶች ቀርጽን ማከናወን ጀመርን። በመጀመሪያው የበጎ አድራጎት ሥራችን ገንዘብ አሰባስበን በሺ የሚቆጠሩ ደብተሮች ገዝተን፣ በደብተሩ ላይ "በኬንያ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተላከ" ብለን ወደ ኢትዮጵያ አምጥተን ለትምህርት ሚኒስቴር ሰጠን፡፡አምጥቼ ለትምህርት ሚኒስቴር የሰጠሁት እኔ ነበርሁ። ላይላካልን ቀረ እንጂ የኢትዮጵያና ኤርትራ የሰላም ጉባኤ ናይሮቢ ላይ በተደረገ ጊዜ የጸሎት ፕሮግራም (Prayer Breakfast) ልናዘጋጅ ነበር። የፈረሰው በኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን መሃል በዚህ ጉዳይ መግባባትና መቀባበል ስላልነበረ ነው። ይህን ያሰብነው "ክርስቲያኖች" ነበርን፡፡ አለመስማማታችን እጅግ በጣም አሳዘነኝ፤ ያከራከረን አንዱ ነገር ጸሎቱ በምን ቋንቋ ሊሆን ነው የሚል ነበር።

በመሃከላችን ያለው ዋና አደራዳሪ የቀድሞው ያአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር በሚናገረው ቋንቋ መሆን አለበት ብንልም ሌሎች ምክንያቶች እየቀረቡ ስለ መጡ በየጸሎት ቤታችን ይሁን ተባለ። በዚያን ጊዜ በኬንያ በተለያዩ ቦታዎች በአማርኛና በትግርኛ የአምልኮ ፕሮግራሞች ይካሄዱ ነበር፡፡ "የተፈለገው አብረን መጸለያችን ነው" ብልም ሳንስማማ በመቅረታችን የጸሎት ፕሮግራሙ ሳይካሄድ ቀረ። "የምንጸልየው ለሰላም ነው፤ ኤርትራ በመለየቷ ሰላም የሚመጣ ከሆነ ብንለያይም ግድ የለኝም" ማለቴን አስታውሳለሁ።

ከስብሰባው ስንወጣ ይህን በማለቴ አንድ ኢትዮጵያዊ አዛውንት እንዴት እንደዚህ ትላለህ? ማለት አልነበረብህም አሉኝ፡፡ አንዲት 'ኤርትራዊት' ግን ይህን በማለቴ መደሰትዋን ነግራኝ ነበር። ይህን በምጽፍበት በአሁኑ ጊዜ እንዲህ ያለቺኝ ሴት ያለቺው ጀርመን አገር መሆኑን እሰማለሁ፡፡ እንደ እርሷ ያሉት በኤርትራ ዉስጥ የሉም፤ እርሷም ሆነች ሌሎች የኤርትራን መገንጠል





የፈለጉ ደርግ አስመራን ለቆ ሲወጣ፡ ሻዕቢያ አስመራ እንደገባ ወደ እዚያው ሄደው ነበር፤ እዚያ አልቆዩም፡፡ የተመኙት አልተፈጸመላቸውም፡፡ ኢትዮጵያና ኤርትራ እንደ መልካም ጎረቤት አብረው ሊኖሩ ካለመቻላቸውም በላይ ጥለኞች ሆኑ፡፡ ሲሆን ሲሆን ሁለቱ አንድ አገር ሆነው አልያም እንደ አሜሪካና ካናዳ መልካም ጎረቤታማዎች ሆነው እንዲኖሩ ምኞት ነበረን። እንግዲህ ይህን መጽሃፍ እስከፃፍኩበት እስካሁኑ ሰዓት ድረስ የተመኘነው ሳይሆን ቀርቷል፡፡



የቤተሰብ ፎቶግራፍ በ1980 ዓ.ም. አክላሆማ ሲቲ



የቤተሰብ ፎቶግራፍ በ፲፱፻፹ ዓ.ም. ኦክላሆማ ሲቲ